ው ፡ እንደዚኽ ፡ ነው ፤ ባንዱ ፡ የኹሉ ፡ ይታወቃል ። ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ ደግሞ ፡ አልና ፡ ነበር ፡ ሲስቡት ፣ ወይም ፡ ሲዘምቱበት ፡ ጎላፊነቱ ፡ በ፪ ፡ ጽንዕ ፡ ይፈታል ፤ ጽንዕ ፡ ማለትም ፡ ጥናት ፡ ጥ ኦንት ፡ ጥንካሬ ፡ ማለት ፡ ነው ። ባላፊ ፡ ጊዜና ፡ ባላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ይዐይነት ፡ ክፍል ፡ አለ ፤ ዐወቀ ፤ ያኹን ፡ የቅርብ ፣ የዛሬ ፡ የትላንት ፣ ጥቂት ፡ የቂየ ። ዐውቋል ፤ የዋለ ፡ ያደረ ፣ የስንበተ ፡ የዘገየ ። ዐውቆ ፡ ነበር ፤ ፈጽሞ ፡ ያለፈ ፡ የኖረ ፣ ወይም ፡ ያረጀ ፡ የቀረ ። የትንቢቱም ፡ ጊዜ ፡ ክፍሉ ፡ እን ደ ፡ ጎላፊው ፡ ነው ፤ ይኽውም ፡ ይከፍል ፤ ይከፍላል ፤ ይከፍል ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ባንቀጹ ፡ ሦስ ትነት ፡ ይታወቃል ። ርባታው ፡ አሎታ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ አል ፡ ባሎታ ፡ ሞክሼነት ፡ ይቀርና ፣ ነበር ፡ ብቻ ፡ በኹሉ ፡ ይዘምታል ፤ በዘንድም ፡ ፈንታ ፡ እንዲና ፡ ሊ ፡ በራብዕንት ፡ ይገባሉ ። አሎታው ም ፡ አል ፡ ም ፡ ነው ፤ አል ፡ አለ ፡ በቃል ፡ ኹሉ ፡ ሥር ፡ በመነሻ ፤ ም ፡ በጎላፊና ፡ በትንቢት ፡ ጫፍ ፡ ብቻ ፡ መድረሻ ፡ እየኾነ ፡ ይገባል ። (ማስረሻ)

ኢ፡ዐዊቅ ፤ (ኢ፡ያቅ ፣ ኢ፡የዐውቅ ፤ ኢ፡ይውቅ) አለማወቅ ።

(ጎላፊ)	(ትንቢት)	(ዝንድ)	(ትእዛዝ)
አላወቀም ፡ (ነበር)	**አያውቅም ፡ (ነበር)**	**እንዳ(ላ)ያውቅ ፡**	**አይወቅ ።**

(ቅጽልና ፡ ስም)

አላዋቂ ፣ ያላወቀ ፤ የማያውቅ ።

(ቦዝ ፡ አንቀጽ)

(ኢ፡ዐዊቆ ፤ ቃ) ሳያውቅ ፤ ሳታውቅ ።

ግስን ፡ ኹሉ ፡ እንዲኽ ፡ አያልኽ ፡ አርባ ።

ክፍል ፡ ፫ ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

ተረትና ፡ ምሳሌ ፡ ታሪክም ፤ ይኸውም ፡ በባላገር ፡ የሚኖሩ ፡ አባትና ፡ እ ናት ፡ ሕፃናት ፡ አፋቸውን ፡ ከፈቱ ፡ በኋላ ፡ የሚያስተምሯቸው ፡ ነው ።

(ተረት ፡ ተረት ፣ የላም ፡ በረት) ።

(አ)—እውነት ።

**እውነትና ፡ ዕብለት ፡ ውሃና ፡ እሳት ፡ እነዚኽ ፡ አራቱ ፡ ዐብረው ፡ ዘመ ቱና ፡ ያገኙትን ፡ ኹሉ ፡ ማርከው ፡ ዘርፈው ፡ ይዘው ፡ ሲመለሱ ፤ መቼም ፡ አቶ ፡ ዕብለት ፡ ለተንኰል ፡ አያርፍምና ፤ ወደ ፡ ውሃ ፡ ቀርቦ ፡ እንተ ፡ እሳ ትን ፡ ግደለውና ፡ (አጥፋውና) ፤ ያገኘነውን ፡ ኹሉ ፡ ለሦስት ፡ እንካፈላለ ን ፡ ብሎ ፡ መከረው ። ሞኙ ፡ ውሃም ፡ ወደ ፡ ወሰዱት ፡ የሚሄድ ፡ ስለ ፡ ኾ ነ ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ መስሎት ፡ እሳትን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢረጫጠው ፡ ሞተ ፡ (ጠፋ) ። ከዚኽም ፡ በኋላ ፡ አካሄዱን ፡ አይተኽ ፡ ጭብጠዉን ፡ ቀማው ፡ እንዲሉ ፤ ወደውነት ፡ ቀርቦ ፤ እውነት ፡ ከብታችንን ፡ ይዘን ፡ ወደ ፡ ዳገት ፡ አለው ። ውሃም ፡ አሻቅቦ ፡ መውጣት ፡ አይኸንለትምና ፤ ራሱን ፡ ይዘ ፡ እ የጮኸ ፡ ቀልቀል ፡ ሄደ ፡ (ወረደ) ። እውነትና ፡ ዕብለትም ፡ ከብቱን ፡ ኹ ሉ ፡ ነድተው ፡ ወዳገር ፡ ቤት ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አቶ ፡ ዕብለ ት ፡ እውነትን ፡ ከድቶ ፡ ከብቱ ፡ ኹሉ ፡ የኔ ፡ ነው ፣ አንተ ፡ ግን ፡ አሽከ

ሬ ፣ ነኽ ፣ እንጂ ፣ ምንም ፣ የለኽ ፣ አለው ። ስለዚኽም ፣ ተካሰው ፣ በዳኛ ፣ ፌት ፣ ቆመ ፣ ዳኛውም ፣ ሽማግሌ ፣ ይያችኹ ፣ አላቸው ፤ ሽማግሌቹም ፣ ነገሩን ፣ ከመረመሩ ፣ በኂላ ፣ ታገሉና ፣ እውነት ፣ የጣለ ፣ እንደ ፣ ኾነ ፣ ወብራችኹ ፣ ብሉ ፣ (ተካፈሉ) ፤ ያልጣለ ፣ እንደ ፣ ኾነ ፣ ላን ፣ ይቅርበት ፣ አሉ ። በታገሉም ፣ ጊዜ ፣ እውነት ፣ ጣለ ። ስለዚኽ ፣ እውነትና ፣ ዕብለት ፣ ባንድነት ፣ ይኖራሉ ፣ ይዘታውም ፣ የብለት ፣ ይበዛል ፤ የውነት ፣ ግን ፣ እጅግ ፣ ትንሽ ፣ ነው ። እውነቱን ፣ ተናግሮ ፣ እመሸበት ፣ ያድራል ። እውነትን ፣ ግዛት ፣ አትሸጣትም ፤ (ምሳ፳፫ ፣ ፳፫) ። (፩ኛ ፣ ሥዕል)·

አመቴ ፣ (የወንዝ ፣ አመቴ) ። የወንዝ ፣ አመቴ ፣ በወንዝ ፣ የምትውል ፣ የጋጋኖ ፣ ዐይነት ፣ አሞራ ፣ ናት ። ምላቧም ፣ ዓሣና ፣ ያይጥ ፣ ዓሣ ፣ ወይም ፣ እንቁራሪት ፣ ነው ። የምትሠራውም ፣ ቤት ፣ ካንድ ፣ ጐበዝ ፣ ሽክም ፣ ይበልጣል ፤ ስትሠራውም ፣ በባላ ፣ ባልቾ ፣ ዛፍ ፣ ላይ ፣ በስተምዕራብ ፣ በኩል ፣ አፉን ፣ ወደ ፣ ምድር ፣ ታደርገዋለች ፣ ውስጡንም ፣ በጭቃ ፣ ትመርገዋለች ፤ በበት ፣ ትለስነዋለች ። በክረምትም ፣ እንቁራሪት ፣ ልትበላ ፣ ኩሬ ፣ ወዳለበት ፣ ሂዳ ፣ ትውላለች ፤ ያን ፣ ጊዜም ፣ ጭልፌት ፣ እቤቷ ፣ ትገባና ፣ ማታ ፣ በመጣች ፣ ጊዜ ፣ በውስጥ ፣ ኹና ፣ እየነከሰች ፣ ታባርራታለች ። እሷም ፣ በዛፉ ፣ ላይ ፣ ዝናም ፣ ሲወርድባት ፣ ታድራለች ፤ (ከቶም ፣ የወንዝ ፣ አመቴ) ። በማግስቱም ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ሌላ ፣ ቤት ፣ መሥራት ፣ ትዠምራለች ። እንደ ፣ ገዲ ፣ በበጋ ፣ ምግቧን ፣ ሰብስባ ፣ በክረምት ፣ በቤቷ ፣ ብትውል ፣ ቤቷን ፣ ባልተቀማች ፣ ነበር ። ለላመትም ፣ ዐዲሱን ፣ ቤት ፣ ትቀማታለች ።

(በ) — ቡዳ ፤ ወይም ፣ ጠይብ ፣ ወይም ፣ ባለጅ ።

፩ፈላሻ ፣ ወዳገራችን ፣ መጥቶ ፣ ከንጉሥ ፣ ጋራ ፣ ባለሻል ፣ ኾነ ። ምክንያቱም ፣ አንጥረኛ ፣ ስለ ፣ ኾነ ፣ ወርቅና ፣ ብር ፣ እያፈሰሰ ፣ ወልቦና ፣ ድኩት ፣ አንባርና ፣ ቀለበት ፣ ድሪና ፣ ማርዳ ፣ መጣና ፣ ጣፋ ፣ ጫሜ ፤ በ ያይነቱ ፣ ጌጥና ፣ ሽልማት ፣ ዘውድም ፣ ከመሥራቱ ፣ የተነሣ ፣ ነው ። ያም ፣ ንጉሥ ፣ ቀጥቃጮችንና ፣ አንጥረኞችን ፣ ጠይብ ፣ የተባለንም ፣ ኹሉ ፣ እጅግ ፣ ወደዳቸው ፣ ካለቃቸውም ፣ ጋራ ፣ ኹል ፣ ጊዜ ፣ ቂይታ ፣ ያደርግ ፣ ነበር ፤ ካህናትን ፣ ግን ፣ ባይኑም ፣ ለማየት ፣ ጠላ ። ካህናቱም ፣ በጠይቦቹ ፣ እጅግ ፣ ቀኑባቸው ፤ እነሱንም ፣ ለማጥፋት ፣ ተማከሩ ። ከካህናቱም ፣ አንዱ ፣ ደብተራ ፣ ከሰው ፣ ክፉ ፣ ደብተራ ፤ ካውሬ ፣ ክፉ ፣ ዳሞትራ ፣ እንደ ሚሉ ፣ ወደ ፣ ወንዝ ፣ ሂዶ ፣ ጋኔን ፣ ጐተተ ። ጋኔኑም ፣ ለምን ፣ ጠራኸኝ ፣ ቢለው ፣ እነዚኽን ፣ ጠይቦች ፣ ከቤተ ፣ መንግሥት ፣ የሚያሰጣ ፣ እኛን ፣ የሚያስገባ ፣ እነሱን ፣ የሚያስጠላ ፣ እኛን ፣ የሚያሰድድ ፣ ብልጎት ፣ አድር

ግልኝ ፡ አለው ። መቹም ፡ ለሰይጣን ፡ ተንኰል ፡ ቅርቡ ፡ ነውና ፤ ሂጂ ፡ ናን ጉሡን ፡ ልጅ ፡ አሳብዳታለኹ ፤ ምን ፡ ኸንሽ ፡ ያሏትም ፡ እንደ ፡ ኸነ ፡ የ ጠይቦቹ ፡ አለቃ ፡ በላኝ ፡ እያለች ፡ ትለፈልፋለች ። መድኅኒትኽስ ፡ ምንድ ነው ፡ ቢሏትም ፡ ያንተን ፡ ስም ፡ ጠርታ ፡ መድኅኒቴንና ፡ ምሴን ፡ ደብተ ራ ፡ እከሌ ፡ ያውቀዋል ፡ ትላለች ። አንተንም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ይጠሩኻል ፤ የማንኛውንም ፡ ዕንጨት ፡ ሥር ፡ ትቀጠቅጥና ፡ ይዘኽ ፡ መጥተኽ ፡ ታጥና ታለኽ ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ እንደ ፡ ሾጣ ፡ አው ፡ አሰኝቹ ፡ አተላ ፡ አስጠጥቹ ፡ አለቃታለኹ ። ከዚኽም ፡ በኋላ ፡ ጠይቦቹ ፡ ኹሉ ፡ ለብቻቸው ፡ በዋሽ ፡ ይኖራሉ ፡ እንጂ ፡ እቤተ ፡ መንግሥት ፡ አይገቡም ፤ በከተማም ፡ አይቀመ ጡም ፡ (አይኖሩም) ። እናንተ ፡ ግን ፡ ከነገሥታቱ ፡ ጋራ ፡ በለሻሎች ፡ ት ኸናላችኹ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፡ (መከረው) ፤ እንደ ፡ ነገረውም ፡ ኸነ ። ከዚያ ፡ ወዲ ኽ ፡ ጠይቦች ፡ ሰው ፡ ይበላሉ ፡ ይባላል ፤ ጋኔንም ፡ ሥራዉን ፡ (ማታለሉ ን) ፡ ሲሠራ ፡ ይኖራል ። ባረብኛ ፡ ጠይብ ፡ ማለት ፡ ማለፊያ ፡ ደግ ፡ ማለት ፡ ነው ። ቡዳ ፡ ላን ፡ የዣፖንና ፡ የቺንን ፡ ሃይማኖት ፡ ያወጣ ፡ የህንድ ፡ ን ጉሥ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ቡዳ ፡ እጅላ ፡ ብልሳ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከባለቤት ፡ ያወቀ ፡ ቡዳ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ባማርኛ ፡ ጠይብ ፡ የተባለው ፡ በግእዝ ፡ ጠቢብ ፡ ይ ባላል ፤ ብልሳ ፡ ፈላስፋ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይምሰል ፡ አይምሰል ፤ የጠይብ ፡ እጁ ፡ ተከሰል ። (ፎኛ ፡ ሥዕል)

ቢልተኛ ። አንድ ፡ ቢልተኛ ፡ ሰው ፡ በጉን ፡ ሊሸጥ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ይዘ ፡ ሄደ ። በገ በያም ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ በግ ፡ ፈላጊ ፡ መጣና ፡ በዘንጉ ፡ የበጉን ፡ ዠርባ ፡ ነካ ፡ አድርጎ ፡ ባለበ ግ ፡ ቢለው ፤ አይሸጥም ፡ ለዘንግ ፡ አለ ፤ ምን ፡ ይላል ፡ አንተ ፡ ቢል ፤ ባ ፡ ይላል ፤ ምን ፡ የሚ ያፈ ፡ ነው ፤ በጠጥ ፤ ረ ፡ የት ፡ ያደገ ፡ ነው ፤ አ ጋጥ ፤ እንዲኽ ፡ እያለ ፡ ቢያላግጥበት ፡ ተናደደ ና ፡ ጐራዴዉን ፡ ውልቅ ፡ አደረገ ፤ እሱም ፡ አ የንልኽ ፤ ኹለት ፡ ጪው ፡ ያወጣልኻል ፡ አለው ፡ ይባላል ። (ፎኛ ፡ ሥዕል)

(ገ)—ገበሬ ።

ዐጤ ፡ ምኒልክ ፡ ከጐንደር ፡ ከተመለሱ ፡ በ ኋላ ፡ ለጊዜው ፡ ወታደር ፡ በባላገር ፡ ላይ ፡ ይ መራ ፡ ነበርና ፤ የጐንደር ፡ ወታደር ፡ ምሪት ፡ የ ተመራበት ፡ አንዱ ፡ የሸዋ ፡ ገበሬ ፡ ባገዳው ፡ ዳ ር ፡ ያጠመደው ፡ ወጥመድ ፡ ድኩላ ፡ ቢይዝለ ት ፡ ወታደሩ ፡ የሰማ ፡ እንደ ፡ ኸነ ፡ ይቀማኛ ል ፡ ብሎ ፡ ፈራና ፡ ሚስቱን ፡ እንትን ፡ ባልኹ በት ፡ እንትን ፡ ገባበት ፤ እንትን ፡ አምጪልኝ ፡ እንትን ፡ አልበት ፤ አንቺም ፡ ነዪልኝ ፤ እንት ን ፡ ትይልኝ ፡ ብሎ ፡ ድምጥ ፡ ቢያሰማት ፡ ወ ደንጪት ፡ የምትሄድ ፡ መስላ ፡ ገመድ ፡ ጠቅላ ፡ ቢላዋ ፡ ደብቃ ፡ ሄደች ። ማታም ፡ ሥጋዉን ፡ በርጥብ ፡ ሣር ፡ ጠቅለው ፡ ወደ ፡ ጐተራ ፡ ቤት ፡ አገቡት ። እንት ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ በቂ ፡ ይኸ ናልና ፡ ላኹኑም ፡ ዐማርኛ ፡ በቂ ፡ መኸኑ ፡ ነው ። (ፎኛ ፡ ሥዕል)

ጕጕት ። ጕጕት ፡ ፈጣ ፡ በሩቁ ፡ ድመ ት ፡ የሚመስል ፡ አሞራ ፡ ናት ። እሷም ፡ ዐይ ኗ ፡ ከፀሓይ ፡ ብርሃን ፡ ጋራ ፡ አይዋሐድምና ፡ ቀን ፡ በገደል ፡ ላይ ፡ ቊጭ ፡ ብላ ፡ ትውላለች ። ሌሊትም ፡ ወዲያና ፡ ወዲኽ ፡ ስትል ፡ ዐይጥና ፡ ድመት ፡ ብታገኝ ፡ ትበላለች ። ዳግመኛም ፡ የሌ ት ፡ ወፍ ፡ ቀን ፡ ብርሃን ፡ በሌለበት ፡ ቦታ ፡ በ ዋሻ ፡ ወይም ፡ በጣራ ፡ ውስጥ ፡ ላባ ፡ በሌለባቸ ው ፡ በኹስቱ ፡ ክንፎቿ ፡ ቊልቊል ፡ ተዘቅዝ ቃ ፡ (ተንጠልጥላ ፡ ተሰቅላ) ፡ ትውልና ፡ ሌሊ ት ፡ ስትበር ፡ ታድራለች ፤ መብራትም ፡ ያየች ፡ እንደኾን ፡ ለማጥፋት ፡ ትጣጣራለች ። ቦኛም ፡

በክንፎቿ ፡ ውስጥ ፡ ንጽብራቅ ፡ (ብልጭ ልጭ ታ) ፡ ያላት ፡ ስሻና ፡ መልኳ ፡ የማይታወቅ ፡ ሌሊት ፡ ስትበር ፡ ክንዷን ፡ ዕጥፍ ፡ ዘርጋ ፡ ስታደርግ ፡ በክንፎቿ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ንጽብራቅ ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ ይላልና ፤ ባላገሮች ፡ የሰይጣን ፡ መብራት ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤ ከውጪም ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ይገባሉ ። ፱ኛም ፡ ስሻና ፡ መልኳ ፡ የማይታወቅ ፡ ሌሊት ፡ ስትበር ፡ የክንፏ ፡ ድምጥ ፡ እንደ ፡ ተተኰሰ ፡ ርሳስ ፡ የሚሰማ ፡ አንዲት ፡ አሞራ ፡ አለች ፤ እነዚኽ ፡ ከጪለማ ፡ በቀር ፡ ላይናቸው ፡ ብርሃን ፡ የማይሰማ ማቸው ፡ ናቸው ። እንደዚኽም ፡ ኹሉ ፡ በሥጋዊና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ነገር ፡ ክሰት ፡ በቀር ፡ እውነት ፡ የማይሰማማቸው ፡ ሰዎች ፡ ቍጥር ፡ የላቸውም ፤ እነሱም ፡ በጪለማ ፡ ድንቍርና ፡ ይሄዳሉ ፡ (ይኖራሉ) ። እነዚኽም ፡ ላይናቸው ፡ ብርሃን ፡ የማይሰማማቸው ፡ ወሮች ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ ባሜሪካ ፡ አገር ፡ ይደሩ ፤ ሌሊት ፡ ሌሊት ፡ ግን ፡ ባገራችን ፡ ይዋሉ ።

(ደ) — ደም ።

አንድ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ጕራዴዉን ፡ ያለልክ ፡ ሳለና ፡ ስለቱን ፡ ለማየት ፡ በውሻው ፡ ገር ረባ ፡ ላይ ፡ ሳብ ፡ ቢያደርገው ፡ ውሻው ፡ ከኹለት ፡ ክፍል ፡ ብሎ ፡ ሞተ ። እሱም ፡ ለውሻው ፡ ጥቂት ፡ ሳያዝን ፡ እከደክዴ ፡ ጕራዴዬን ፡ የውሻ ፡ ደም ፡ ነካብኝሳ ፡ ብሎ ፡ ጕራዴዉን ፡ ሊያጥብ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ወረደ ፤ በወንዝም ፡ ተቀምጠ ፡ ሲያጥብ ፡ መንገደኞች ፡ ወንድማቸውን ፡ ሽፍታ ፡ ገድሰዋቸው ፡ ጠፍቶ ፡ ነበርና ፤ ያንን ፡ ሽፍታ ፡ ሲፈልጉ ፡ ደም ፡ የነካው ፡ ጕራዴ ፡ ሲያጥብ ፡ ቢያዩት ፡ ይኽ ፡ ነው ፡ ወንድማችንን ፡ የገደለው ፡ ብለው ፡ ደብድበው ፡ ገደሉት ። ከዚኽ ፡ የተነሣ ፡ እግዜር ፡ የውሻን ፡ ደም ፡ እንኳ ፡ አያስቀርም ፡ ይባላል ፤ ስለዚኽ ፡ ላራዊት ፡ መራት ፡ ይገባናል ። ሰው ፡ እንግዳ ፡ ቢኾን ፡ እግዜር ፡ ባላገር ፡ ነው ። (፭ኛ ፡ ሥዕል)

ድመት ። ድመት ፡ ከንበሳና ፡ ከነብር ፡ የተለየ ፡ የቤት ፡ አውሬ ፡ ነው ። ምግቡም ፡ ዐይጥ ፡ ወይም ፡ ሥጋና ፡ ወተት ፡ ዳቦም ፡ ነው ። ዐይጥ ፡ እየያዘ ፡ በልቶ ፡ ከጠገበ ፡ በኋላ ፡ የሚይዘዉን ፡ ዐይጥ ፡ ሲርበው ፡ ሊበላ ፡ እየገደለ ፡ ይጥለዋል ። ዳግመኛም ፡ እንዳይበላ ፡ በመጥገቡ ፡ እንዳይተው ፡ በመሠሠቱ ፡ ዐይጠቹን ፡ ሳይገድል ፡ ኹለት ፡ ዐይናቸውን ፡ አጥፍቶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እያጓኝ ፡ ይጫወትባቸዋል ። በዱር ፡ በበረሓ ፡ ከሚኖሩ ፡ ከወንበይና ፡ ከቀማኛ ፡ ከሽፍታና ፡ ከጋዱ ፡ ተለይቶ ፡ ቤት ፡ ሠርቶ ፡ የሚኖር ፡ ክፉ ባለጠጋ ፡ ድመትን ፡ ይመስላል ። እሱ ፡ ያለደንብ ፡ የድኾችን ፡ ገንዘብ ፡ እየቀማ ፡ ማጥኑን ፡ ከመላ ፡ በኋላ ፡ እንሱን ፡ ማሰር ፡ መግረፍ ፤ መቀማት ፡ መግፈፍ ፡ አይተውምና ፤ በመጨረሻውም ፡ ከግዙቱ ፡ እንዳይወጡ ፡ ከባርነቱ ፡ እንዳያመልጡ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ለድንቍርና ፡ ካልተሰጠ ፡ ለጠላቱ ፡ አይገዛምና ፤ የልብ ፡ ዐይን ፡ የተባለ ፡ ትምርትና ፡ ዕውቀት ፡ ስለሌላቸው ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ሲያደርጋቸው ፡ (ሲጫወትባቸው) ፡ ይኖራል ። (ምሳ፴ ፡ ፲፬) ። ያይጥ ፡ ሞት ፡ የድመት ፡ ስርግ ፡ ነው ።

(፯ኛ ፡ ሥዕል)

ደንቈሮዎች ። አንዲት ፡ ደንቈሮ ፡ ሴት ፡ ፍየሎቿ ፡ ቢጠፉባት ፡ ልጇን ፡ ዐገለ ፡ ልትፈልጋቸው ፡ ሄደች ። በመንገድም ፡ አንድ ፡ ደንቈሮ ፡ ገበሬ ፡ ሲያርስ ፡ አላኝታ ፡ ብትጠይቀው ፡ ምንም ፡ ጕሮው ፡ ባይሰማ ፡ ባለፍየል ፡ መኾኗን ፡ ያውቃልና ፤ ፍየሎቿ ፡ ያሉበትን ፡ በጁ ፡ አመለከታት ። እሷም ፡ ወዳመለከታት ፡ ሂዳ ፡ ፍየሎቿን ፡ አግኝታ ፡ ስትመለስ ፡ አንዱን ፡ ወጠጤ ፡ እግሩን ፡ ናዳ ፡ ስለ ፡ ሰበረው ፡ ብድር ፡ የመለሰች ፡ መስሏት ፡ ይኽን ፡ ወጠጤ ፡ ዐርደኽ ፡ ብላ ፡ አለችና ፡ ብትሰጠው ፡ ያልሰማ ፡ ጕሮ ፡ ከጎረ ፡ ቤት ፡ ያጣላል ፡ እንደሚሉ ፡ ፍየሌን ፡ የሰበርኽው ፡ አንተ ፡ ነኽ ፡ ማለቷ ፡ መሰለውና ፡ ሊመታት ፡ ፈለገ ፤ በዚኽም ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ሂደው ፡ ተቋቋሙ ። ለዳኛዉም ፡ እንዲኽ ፡ ብሎ ፡ አሳየ ፤ እግዚሓር ፡

ያሳይዎ ፤ ክርስቶስ ፥ ያመልክትዎ ፥ ጌታዬ ፤ ይኸች ፥ ሴት ፥ ፍየሎቿ ፥ ጠ
ፍተዉበት ፥ ባሳያት ፥ ወጠጤዬን ፥ የሰበርኸው ፥ አንተ ፥ ነኽ ፥ ብላ ፥ ያዘች
ኝ ። እሷም ፥ እግዚሓር ፥ ያሳይዎ ፤ መልአኩ ፥ ያመልክትዎ ፤ ይኽ ፥ ሰው ፥
ፍየሎቹ ፥ ያሉበትን ፥ ስላመለከተኝ ፥ አንድ ፥ ናዳ ፥ የሰበረው ፥ ወጠጤ ፥
ወስደኽ ፥ ብላ ፥ ብዬ ፥ ብሰጠው ፥ ሊመታኝ ፥ ተጋበዘብኝ ፥ አለችና ፥ አመ
ለከተች ። ዳኛውም ፥ ደንቂሮ ፥ ነበርና ፤ ልጅ ፥ ማዘሏን ፥ አይቶ ፤ አያችኹ ፥
አያችኹ ፥ ይኽ ፥ ልጅ ፥ ቀኒጥ ፥ እሱኑ ፥ ይመስላል ፤ በል ፥ ቀለቧን ፥ ስፈ
ር ፥ ብሎ ፥ በየነበት ፥ ይባላል ።

(ወ) — ውሻ ።

ውሻ ፥ ክኹብና ፥ ክተኵላ ፥ ክቀበሮም ፥ የ
ተለየ ፥ የቤት ፥ አውሬ ፥ ነው ። ምግቡም ፥ ሥ
ጋና ፥ እንጀራ ፥ ነው ። ባንድ ፥ ቤት ፥ ኹለት ፥
ውሾች ፥ ቢኖሩ ፥ አንዱ ፥ ሥጋ ፥ ያገኘ ፥ እንደ ፥
ኽነ ፥ ላንዱ ፥ አይሰጥምና ፤ ርስ ፥ በርሳቸው ፥ ይ
ጣላሉ ፤ ይናከሳሉ ። ጩኸታቸውንም ፥ ሰምቶ ፥
ሌላ ፥ ውሻ ፥ ከውጪ ፥ ይመጣል ፤ ሥጋዉንም ፥
ይወስደዋል ። እንደዚኽም ፥ ኹሉ ፥ ርስ ፥ በር
ሳቸው ፥ የሚጣሉ ፥ ሰዎች ፥ እነሱን ፥ ይመስላሉ ፤
ንጻነታቸውንም ፥ ያሶስዳሉ ።

የውሻ ፥ ዕወቀት ። በተጕለት ፥ ማገ
ዋሽ ፥ በሚባል ፥ አገር ፥ መምሬ ፥ ሀብትኽ ፥ ይ
መር ፥ የሚባሉ ፥ ቁስ ፥ ነበሩ ። እሳቸውም ፥ ከ
ሰው ፥ ጋራ ፥ ተጣልተው ፥ ሲነጋገሩ ፥ ውሻቸው ፥
የባለጋራቸውን ፥ ባቱን ፥ ነከሰው ። በወግዳ
ም ፥ በደኞች ፥ ጋረደው ፥ ቤት ፥ የንግዳ ፥ ሰው ፥
ዕቃና ፥ በትር ፥ እያሸተተ ፥ ባሱ ፥ ወደ ፥ ውጪ ፥
አውጥቶ ፥ የሚጥል ፥ አንድ ፥ ውሻ ፥ ነበረ ። ባ
ለቤቱን ፥ ካልናቁ ፥ ውሻዉን ፥ አይመቱ ።

(፷ኛ ፥ ሥዕል)

(ዘ–ዠ) — ዥጉብ ።

ዥጉብ ፥ በዱር ፥ የሚኖር ፥ የውሻና ፥ የቀበ
ሮ ፥ የተኵላም ፥ ዐይነት ፥ አውሬ ፥ ነው ። ምግ
ቡም ፥ ሥጋ ፥ ነው ። እሱም ፥ ጕልበተ ፥ ብር
ቱ ፥ ልበ ፥ ፈሪ ፥ ይባላል ። ካንይሱም ፥ ብዛት ፥
የተነሣ ፥ እማጥ ፥ የገባዉን ፥ አህያ ፥ ባለቤቶቹ ፥
ማውጣት ፥ አቅቷቸው ፥ ደፍጠው ፥ ሲጠብቁ ፥
ከማጡ ፥ ውስጥ ፥ በደንደሱ ፥ አውጥቶ ፥ በወረ
ወረው ፥ ጊዜ ፥ አስጥለው ፥ ወሰዱት ፥ ይባላል ።
ዥጉብ ፥ ሆዳም ፥ ነው ፤ ማታ ፥ ከጕሬው ፥ በወ
ጣ ፥ ጊዜ ፥ ብክካዉንም ፥ እበቱንም ፥ ይበላል ፤
ስለዚኽ ፥ ዐሩ ፥ ነጭ ፥ ነው ። ያረጀውንና ፥ የደ
ከመውንም ፥ ዥጉብ ፥ ይጠራል ። እንደ ፥ ምን ፥
ቢሉ ፥ ያለመጠን ፥ በልቶ ፥ ይመጣና ፥ ያስታው
ክለታል ፤ ጢት ፥ አላደርስ ፥ ብሎት ፥ (አፋጠት) ፥
በዋሻው ፥ አጠገብ ፥ ያስታወከውን ፥ ባገሬ ፥ አ
ይቻለኹ ። ቡችሎቹንም ፥ ሲያሳድግ ፥ እንደዚ
ኹ ፥ ነው ። ውሾችም ፥ ለቡችሎቻቸው ፥ እንደ
ዚኹ ፥ ያደርጋሉ ፥ (ያስታውክሉ) ። እንደ ፥ ዥጉ
ብ ፥ ጕልበተ ፥ ብርቱ ፥ ኹኖ ፥ ልበ ፥ ፈሪ ፥ መ
ኽን ፥ አይገባም ። ዥጉብ ፥ ያህያ ፥ ጠላት ፥ ነው
ና ፤ አንድ ፥ ቀን ፥ ማታ ፥ አህያዋ ፥ እገደል ፥ አ
ፋፍ ፥ ወልዳ ፥ ቢያገኝ ፥ ከደስታው ፥ ብዛት ፥ የ
ተነሣ ፥ ሙቤ ፥ ሲዘል ፥ ገደል ፥ ገባ ፥ ይባላል ።
ዥጉብ ፥ አያውቁት ፥ አገር ፥ ሂደ ፥ ቄርበት ፥ አን
ጥፉልኝ ፥ ይላል ። እንደዚኽም ፥ ኹሉ ፥ ክፉ ፥
ሰው ፥ ክፋቱን ፥ በማያውቁበት ፥ አገር ፥ ይከብ
ራል ።

(፷ኛ ፥ ሥዕል)

ዘንዶ ። ዘንዶ ፥ የሰውና ፥ የንስሳ ፥ ያራ
ዊት ፥ የፍጥረትም ፥ ኹሉ ፥ ጠላት ፥ ነው ። እን
ዚኽንም ፥ ይዘ ፥ ለመብላት ፥ አስቀድሞ ፥ በዛ
ፍ ፥ ላይ ፥ ተጠምጥሞ ፥ ይቈይና ፥ በዛፉ ፥ ሥ
ር ፥ የሚያልፉትን ፥ ኹሉ ፥ በዥራቱ ፥ እየያዘ ፥
ይልሳቸዋል ፤ ይውጣቸዋልም ። እስ ም ፥ ከነገ
ሥታትና ፥ ከመኳንንት ፥ ተጠግተው ፥ ድኾችን ፥
የሚበድሱና ፥ ገንዘባቸውን ፥ የሚቀሙ ፥ ክፉዎ
ች ፥ ሰዎችን ፥ ይመስላል ። ዳግመኛም ፥ በተረ
ት ፥ ዘንዶ ፥ ከባሕር ፥ ላይ ፥ ተኝቶ ፥ ጨዛ ፥ ይ
ልሳል ፥ ይባላል ። ይኽም ፥ ተረት ፥ ባለጠጋ ፥ም
ንም ፥ ሀብታም ፥ ቢኾን ፥ የድኾችን ፥ ገንዘብ ፥
መቀማት ፥ አለመተዉን ፥ ያስረዳል ። ቮኛም ፥
በኦሪት ፥ ዘፍጥረት ፥ እንደ ፥ ተጣፈ ፥ አባብን ፥ል
ቡን ፥ አይቶ ፥ እግር ፥ ነግው ፥ ይባላል ። እግዜ
ርም ፥ የባለጠጋን ፥ ክፋቱን ፥ አይቶ ፥ የሰበሰበዉ

ን ፣ እንዳይበላ ፣ ያደርገዋል ። (መዝ፴፱ ፣ ፮ ። ፸፱ ፣ ፲) ። ዓሣ ፣ ጐርጓሪ ፣ ዘንደ ፣ ያወጣል ፤ የሰው ፣ ፈላጊ ፣ የራሱን ፣ ያጣል ። እባብ ፣ ግደል ፣ ከንበትሩ ፣ ገደል ። (፲፫ ፣ ሥዕል)

ዝንጀሮ ። ዝንጀሮ ፣ እንደ ፣ ጦጣ ፣ የሰው ፣ ኹናቴ ፣ ያለው ፣ የዳር ፣ አውሬ ፣ ነው ። በመልክም ፣ ኹለት ፣ ዐይነት ፣ ስለ ፣ ኾነ ፣ ነጨናኝ ፣ ጥቍሬ ፣ ይባላል ። ጥቍሬው ፣ ዝንጀሮ ፣ እጅግ ፣ ቀናተኛ ፣ በመኾኑ ፣ እንደ ፣ ክፉው ፣ ፈርዖን ፣ ተባት ፣ ሲወለድ ፣ ይገድላልና ፣ ተባት ፣ የወለደች ፣ ዝንጀሮ ፣ ሙጫሊዉን ፣ በሆዷ ፣ ዐዝላ ፣ (ለጥፋ) ፣ ነው ፣ የምትሄደው ፤ ስትሄድም ፣ ዳር ፣ ዳሩን ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ከጅሩ ፣ ወይም ፣ ከጨውቴውና ፣ ከጭላዳው ፣ መኻል ፣ ገብታ ፣ አትሄድም ። ተባት ፣ ተባቱም ፣ ካደገ ፣ በኋላ ፣ እየተለየ ፣ ሰባት ፣ ሰባት ፣ ኹኖ ፣ ለብቻው ፣ ይጮራል ፣ (ይሰማራል) ። ስሙም ፣ ቦለዴ ፣ ይባላል ። ከዚኽም ፣ በኋላ ፣ ስፍራ ፣ ሲመቸው ፣ የታዘለችውን ፣ እንስት ፣ ሙጫሊት ፣ ከናታ ፣ ገርባ ፣ ነጥቆ ፣ (ነጥሎ) ፣ ይወስድና ፣ እያዘለ ፣ አሳድጎ ፣ በጊዜዋ ፣ ያውቃታል ፣ (ይደርስባታል) ። ነጥቆ ፣ መውሰዱንና ፣ ዐዝሎ ፣ ማሳደጉን ፣ ባገሬ ፣ አይቻለኹ ። ከነዚያም ፣ ከሰባቱ ፣ ቦለዶች ፣ በየጊዜው ፣ ያሽንፈ ፣ ይወስዳታል፤ ትንሹ ፣ ዝንጀሮ ፣ የትልቁን ፣ ጫማ ፣ ይለካልና ። ወይም ፣ ጎይል ፣ ቢያገኝ ፣ የትልቁን ፣ ገመር ፣ (ያባቱን) ፣ ጅር ፣ ይቀማል ። ጥቍሬው ፣ ዝንጀሮ ፣ ከፈሪነቱ ፣ ብዛት ፣ የተነሣ ፣ በሰፈረበት ፣ ገደል ፣ ሥር ፣ ኹኖ ፣ ነብር ፣ ድምጡን ፣ ቢያሰማው ፣ ካይኑ ፣ ጭፋር ፣ እንባው ፣ እያቀረረ ፣ ከገደሉ ፣ እየተንከባለለ ፣ ይወድቃል ። ነጨው ፣ ዝንጀሮ ፣ ግን ፣ ነብርን ፣ አይፈራም ፤ ቀን ፣ ለቀንም ፣ ቢመጣበት ፣ አባሎ ፣ እየቈረጠ ፣ ይደበድበዋል ። ስለዚኽ ፣ ነብር ፣ ነጨ ፣ ዝንጀሮ ፣ ቢያይ ፣ በደኑ ፣ ውስጥ ፣ ድምጡን ፣ አጥፍቶ ፣ ይውላል ። የነጩም ፣ ዝንጀሮ ፣ ስም ፣ እንዳሞድ ፣ ይባላል ። እንዳመድ ፣ ያለ ፣ ማለት ፣ ነው ፤ ወይም ፣ እንዳፍንጣ ፣ ዐሻዳው ፣ ጥቍሬ ፣ ዝንጀሮ ፣ ያለ ፣ ማለት ፣ ይኸናል ። ይኽም ፣ እንዳሞድ ፣ የሰው ፣ የሚመስሉ ፣ ኹለት ፣ ሥራዎች ፣ አሉት ። ልኖው ፣ ክረምት ፣ ገብቶ ፣ ሣር ፣ ባደገ ፣ ጊዜ ፣ ጤዛ ፣ የምትጥስ ፣ እንዲት ፣ እንዳሞድ ፣ ያደርጋል ፣ እንጂ ፣ እንዳሞዱ ፣ ኹሉ ፣ ጤዛ ፣ እየጣሰ ፣ አይሄድም ። ያች ም ፣ ተመላልጣ ፣ ስትሞት ፣ ሌላዪቱን ፣ ይተካል ። ስለዚኽ ፣ የተመላለጠች ፣ እንስተኛ ፣ እንዳሞድ ፣ ከጅሩ ፣ መኻል ፣ አትታጣም ። ፱ኛም ፣ ማሽላ ፣ ይቀጥፍ ፣ ይቀጥፍና ፣ እንዳሞዱ ፣ ኹሉ ፣ ተሰብስቦ ፣ ባንድነት ፣ ይቀመጣል ፤ እንዲቷም ፣ እንዳሞድ ፣ በመኻላቸው ፣ ተቀምጣ ፣ እንዳንድ ፣ ራስ ፣ ማሽላ ፣ እያንሣች ፣ ትይዝላቸዋለች ፤ እነሱም ፣ እየገሸነጠፉ ፣ (እየገመገጡ) ፣ ይበላሉ ። ከጥቍሬው ፣ ዝንጀሮ ፣ ይልቅ ፣ ለነጨው ፣ ዕውቀት ፣ አለው ። ለነብር ፣ ጠላታችን ፣ እንደ ፣ ነጨው ፣ እንጂ ፣ እንደ ፣ ጥቍሬው ፣ መኾን ፣ አይገባም ። ነጨው ፣ በግና ፣ ፍየል ፣ እሬትና ፣ ቍልቋል ፣ ይበላል ። ትንሽ ፣ ልጅም ፣ ቢያገኝ ፣ ገፍቶ ፣ ገደል ፣ ይስዳል ። ጥቍሬው ፣ ሙጫሊቷን ፣ ነጥቆ ፣ እንደ ፣ ወሰደ ፣ አባት ፣ እናቷ ፣ ሳይፈቅዱ ፣ ልጃገረድን ፣ ነጥቆ ፣ የወሰደ ፣ ሰው ፣ ዝንጀሮን ፣ ይመስላል ። የዝንጀሮ ፣ ጉሥ ፣ እሱው ፣ ይከምር ፤ እሱው ፣ ያፈርስ ። ከዝንጀሮ ፣ ቁንገፖ ፣ ምን ፣ ይመራርጧል ።

(፲፭ኛ ፣ ሥዕል)

(ጠ) — ጦጣ ። ጦጣ ፣ እንደ ፣ ጕሬዛ ፣ ከዛፍ ፣ ወደ ፣ ዛፍ ፣ የምትዘል ፣ እኽልና ፣ የዛፍ ፣ ፍሬ ፣ የምትበላ ፣ የሰው ፣ ኹናቴ ፣ ያላት ፣ የዱር ፣ አውሬ ፣ ናት ። ማደሪያዋም ፣ በገደልና ፣ በዛፍ ፣ ላይ ፣ ነው ። በተረትም ፣ ከራዊት ፣ ኹሉ ፣ ይልቅ ፣ ብልጥ ፣ ናት ፣ ይሏታል ፤ ተረቱም ፣ ይኽ ፣ ነው ። ጦጣና ፣ ድመት ፣ ባንድ ፣ ቤት ፣ ሲኖሩ ፣ ባለቤቶቹ ፣ በሌሉበት ፣ ጊዜ ፣ ጦጣ ፣ ድመትን ፣ እንቅልፍ ፣ እንደ ፣ ያዛት ፣ አይታ ፣ ርኀዒን ፣ ጠጣችና ፣ የራሷን ፣ አበሳ ፣ በሰው ፣ አብሳ ፣ እንደሚሉ ፤ የድመቷን ፣ አፍ ፣ ለይምሰል ፣ በርን ፣ ቀባችው ፣ ይባላል ። ይኽም ፣ ነገር ፣ ሰው ፣ የሠራዉን ፣ ኀጢ

አት ፡ በሰው ፡ ለማመካኘቱ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። (ዘፍ፲ ፡ ፲፱–፲፫) ። ጠጣን ፡ በ ብልጠት ፡ ተማሪ ፡ ብቻ ፡ በለጣት ፡ ይላሉ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ጠጣ ፡ ቀለሙ ን ፡ ብታፈስበት ፡ ተማሪ ፡ ቢላዋ ፡ ሳለ ፡ ሳለና ፡ በደንደሱ ፡ ወንገቱን ፡ ከር ከር ፡ ከርከር ፡ አድርጎ ፡ ቢላዋዉን ፡ ጥሎት ፡ ሄደ ፤ እሷም ፡ እንደሱ ፡ አ ደርጋለኹ ፡ ብላ ፡ ወንገቷን ፡ በስለቱ ፡ ዐርዳ ፡ ሞተች ። ይኽም ፡ ተረት ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ትምርትና ፡ ዕውቀት ፡ ለሌላቸው ፡ መሣሪያ ና ፡ የተንኰል ፡ ምክር ፡ እየሰጡ ፡ በልማዳቸውና ፡ በሃይማኖታቸው ፡ በገ ዛ ፡ እጃቸው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንዲያጠፍቸው ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። ስለ ፡ ጠ ጣ ፡ አጥፊነትም ፡ ከጠጣ ፡ የዋለ ፡ ጕሬዛ ፡ እኽል ፡ በልቶ ፡ (ፈጅቶ) ፡ ገበ ፡ ይባላል ። (ፎነገ ፡ ፲፫ ፡ ፲፱) ። ሽማግሌ ፡ ኹኖ ፡ ሳለ ፡ የልጆችን ፡ ሥራ ፡ የ ሚሠራዉንም ፡ ሰው ፡ እኸሌ ፡ የጠጣ ፡ ሽማግሌ ፡ ነው ፡ ይሉታል ። ጠጣ ፡ ተይዛ ፡ ትዘፍን ። ጠጣ ፡ በለቤቷን ፡ ታሰጠ ። (፲፱ኛ ፡ ሥዕል)

ጠንቋይ ።

በወግዳ ፡ በራስ ፡ ጕበና ፡ ከተማ ፡ አቅራቢ ያ ፡ አንድ ፡ ጠንቋይ ፡ (ጠንቅ ፡ ዋይ) ፡ ነበረ ። ሚስቱም ፡ በየጊዜው ፡ ስዉን ፡ ኹሉ ፡ ሲያታል ል ፡ እያየች ፡ እጅግ ፡ ዐዘንች ። ከዕለታትም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የባሏ ፡ ባልጌደራ ፡ ሌላ ፡ ጠንቋ ይ ፡ ባሏን ፡ ሊጠይቅ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ መጣ ፤ ባ ሏ ፡ ግን ፡ ጋላ ፡ ዐማራዉን ፡ ሊያታልል ፡ ወ ደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ሄደ ፡ ነበርና ፡ ለጊዜው ፡ በቤ ቱ ፡ አልተገኘም ። ይኽም ፡ ጠንቋይ ፡ እኽል ፡ ውሃ ፡ አቅርባለት ፡ ከተጋበዘ ፡ በኋላ ፡ ዐዲስ ፡ ልብስ ፡ ስትታጠቅና ፡ ስታጣፋ ፡ ቢያያት ፡ ምን ው ፡ እመት ፡ እከሊት ፡ ወዴት ፡ ትሄጃለሽ ፡ አ ላት ፤ እሷም ፡ ካዴ ፡ ዘመቻ ፡ ተመልሶ ፡ የሞ ተ ፡ አባቷን ፡ በሞተ ፡ ባ፲፭ ፡ ዓመቱ ፡ አባትሽ ፡ ታሻልና ፡ በንፍሱ ፡ ድረሺ ፡ የሚል ፡ ጠሪ ፡ መ ጥቶብኝ ፡ ወደ ፡ ሳላይሽ ፡ መሄዴ ፡ ነው ፡ አለ ችው ። እሱም ፡ እስቲ ፡ ቁዩ ፤ መጣፍ ፡ ልይል ሽ ፡ አለና ፡ መጣፉን ፡ ገለጥ ፡ አድርጎ ፡ አይቶ ረ ፡ ጕድ ፡ ረ ፡ ጕድ ፡ አለ ፤ እሷም ፡ ምን ፡ አ ዩ ፡ አለችው ፤ ከቤቱ ፡ በታች ፡ ትልቅ ፡ ዛፍ ፡ የለሞይ ፡ አላት ፤ አዎን ፡ አለ ፡ አለችው ፤ እን ኪያስ ፡ ባውራ ፡ ተሲያት ፡ ውሃ ፡ ሊያጠጣ ፡ ከ ብቶቹን ፡ ይዞ ፡ ሲወርድ ፡ ከዛፉ ፡ ሥር ፡ ተን ሥቶ ፡ ነው ፡ የወጋው ። ዐምና ፡ ቢኽን ፡ ይሞ ት ፡ ነበር ፤ ዘንድሮ ፡ ግን ፡ ሐራ ፡ ዘመኑ ፡ ስባ ት ፡ ወጥቶለታልና ፤ አይዞሽ ፡ አይሞትም ። ዕን ቺ ፡ ግማሹን ፡ ከቅቤ ፡ ጋራ ፡ ቅቢው ፤ ግማሹን ፡ ዕጠኚው ፡ ብሎ ፡ ኹለት ፡ የተቁጣጠረ ፡ ነገር ፡ ሰጣት ። ከዚኽም ፡ በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደሚያ ታልልበት ፡ ሄደ ። ከሚያታልልበትም ፡ አገር ፡ ተመልሶ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በጎረ ፡ ቤት ፡ ቢጠይ ቅ ፡ ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አልሰማንም ፡ አሉ ት ፤ እቤቷም ፡ ገብቶ ፡ አባትሽ ፡ እንደ ፡ ም ን ፡ ኾነ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። እሷም ፡ የሚታጠ ንዉን ፡ ዐጠንኹት ፤ የሚቀባዉንም ፡ ቀባኹት ፡ (ለቀለቅኹት) ፤ ከዚኽ ፡ በኋላ ፡ በርስም ፡ ው ቃቢ ፡ ዳነልኝ ፡ (በጎ ፡ ኾነልኝ) ፡ አለችና ፡ ጫ ማዉን ፡ ሳመችው ። ጥፈትም ፡ ጥፎ ፡ ሰጥቷ ት ፡ ነበርና ፤ ዋጋዉን ፡ ኹለት ፡ ጨው ፡ አም ጪ ፡ አላት ፤ አባቴ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ድኗል ፤ ጥ ፈት ፡ ምን ፡ ያደርግለታል ፡ ብላ ፡ ጥፈቱን ፡ መ ለስችለት ። ያንንም ፡ ጥፈት ፡ ይዞ ፡ ባጣራ ፡ ሚ ካኤል ፡ ደብተራ ፡ ገብረ ፡ ስንበት ፡ የሚባሉ ፡ ዐይን ፡ ስዉር ፡ ነበሩና ፤ ወደሳቸው ፡ ቤት ፡ ሄ ደ ። ጥፈቱን ፡ ልኃቸው ፡ ተቀብሎ ፡ ሲያነበው ፡ ሰምተው ፡ ረ ፡ በሚካኤል ፤ ሰውዬው ፡ በሞተ ፡ ባ፲፭ ፡ ዓመቱ ፡ (አድጎና ፡ ለገብርከ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ) ፡ እያልኽ ፡ ትጥፋለኽን ፤ ያች ፡ ሴት ፡ አላግጣብኻለች ፡ እያሉ ፡ ሳቁበት ። እሱም ፡ ዐ ፍሮ ፡ ወዳገሩ ፡ ወደ ፡ ጕሽውሃ ፡ ተሻገረ ። የ ጠንቋይም ፡ ዋና ፡ ሥራው ፡ ከታላቅ ፡ ማዕረ ግ ፡ ትደርሳለኽ ፤ ሹመት ፡ ሽልማት ፡ ታገኛለ ኽ ፤ ራስ ፡ ይኾገሣች ፡ ትባላለኽ ፡ እያለ ፡ ሰዉ ን ፡ ኹሉ ፡ ሲያስገብርና ፡ ሲያከስር ፡ መኖር ፡ ነው ። ሹመት ፡ ፈላጊም ፡ እሾማለኹ ፡ እያለ ፡

ለጠንቋይ ፡ ሲገብር ፡ ይሞታል ፤ ከነፍሱም ፡ ከ ገንዘቡም ፡ ሳይኾን ፡ ይቀራል ። (ጠንቋይ ፡ ለ ራሱ ፡ አያውቅም) ።

(የ) — ያሬድ ።

ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ዜማን ፡ የደረሰ ፡ ያገራች ን ፡ ሊቅ ፡ ነው ። በትውልዱም ፡ ጌጌዎን ፡ ስ ሚባል ፡ ያኵስም ፡ ገበገ ፡ የቱ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ይባላል ። እሱም ፡ እተማሪ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ት ምርት ፡ ሳይገባው ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፤ በሰ ባተኛውም ፡ ዓመት ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ ኰበለለ ና ፡ ጠፍቶ ፡ ሄደ ፤ በዋሻም ፡ ተቀመጠ ። በዋሻ ውም ፡ አጠገብ ፡ ዛፍ ፡ ነበርና ፡ በዛፉ ፡ ሥር ፡ ቍጭ ፡ ብሎ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ትል ፡ ከዛፉ ፡ ላ ይ ፡ ወጣና ፡ እወገቡ ፡ ሲደርስ ፡ ወደቀ ፤ ዳግመ ኛም ፡ ወጣ ፤ ወደቀ ፤ እንዲኽ ፡ እያደረገ ፡ ስ ድስት ፡ ጊዜ ፡ ወድቆ ፡ በሰባተኛው ፡ ወጣና ፡ የዛፉን ፡ ፍሬ ፡ በላ ። ቅዱስ ፡ ያሬድም ፡ ይኽ ን ፡ የትሉን ፡ ትጋት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ተማ ሪ ፡ ቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ መምሩን ፡ አጥፍቻለኹ ና ፡ ማረኝ ፡ አለው ። ከዚኽም ፡ በኋላ ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ገልጦለት ፡ ዜማን ፡ ደረሰ ። ከዕ ለታትም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከቤተ ፡ ክሲያን ፡ ገብቶ ፡ ሲያዜም ፡ ዜማዉን ፡ ለመስማት ፡ ዐጤ ፡ ገብ ረ ፡ መስቀል ፡ ባጠገቡ ፡ ቆመ ። ንጉሡም ፡ ሳ ያይ ፡ በሰንደቁ ፡ ዐንካሴ ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድን ፡ ጫማ ፡ ወግዶት ፡ ኑሮ ፡ ስንደቁን ፡ ቢነቅለው ፡ ደሙ ፡ ፊን ፡ አለ ፤ ንጉሡም ፡ ደነገጠ ፤ ለቅዱ ስ ፡ ያሬድ ፡ ግን ፡ ከዜማው ፡ ጣዕም ፡ የተነሣ ፡ ምንም ፡ አልተሰማውም ። ጥቂትም ፡ እንኳ ፡ እንዳልተነካ ፡ ዜማዉን ፡ ያዜም ፡ ነበር ፡ እን ጂ ። ንጉሡም ፡ ያልኸውን ፡ እሰጥኻለኹና ፤ ን ገረኝ ፡ አለው ፤ ቅዱስ ፡ ያሬድም ፡ ሌላ ፡ ምን ም ፡ የምፈልገው ፡ ነገር ፡ የለኝም ፤ ሂጂ ፡ ካን ተራራ ፡ (ጊሒት) ፡ ዘንድ ፡ እንድቀመጥ ፡ ፍቀድ ልኝ ፡ አለው ። ፈቀደለት ፤ በዚያውም ፡ ተራራ ፡ ዘንድ ፡ ተቀምጦ ፡ ሲያዜም ፡ ኖረና ፡ ዐረፈ ፡ (ሞ ተ ፤ ተለየ) ። ተማሮች ፡ (ሕፃናት) ፡ ሆይ ፤ ትም ርት ፡ ሳይገባን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቈየን ፡ ብላችኹ ፡ አትዘኑ ፤ ተግታችኹ ፡ ሳትሰለቹ ፡ ተማሩ ፡ እን ጂ ። ፊደል ፡ ክልቴጠረ ፡ ባላገር ፡ በተማሪ ፡ ቤ ት ፡ የኖረና ፡ የተጕላላ ፡ እንዳሻል ፡ ዕወቁ ፤ አ ንድ ፡ ነገር ፡ ሳያውቅ ፡ አይቀርምና ።

(፲፫ኛ ፡ ሥዕል)

(ከ) — ክህነት ።

ከግራኝ ፡ ወዲኽ ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ስለ ፡ ሄደ ፤ ጳጳሱና ፡ መምራኑም ፡ የሚገኙት ፡ በጐንደር ፡ ከመኾኑ ፡ የተ ነሣ ፡ የክርስቲያን ፡ ትምርት ፡ ዛሬ ፡ የጋላ ፡ ቤት ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ጠፋ ። በጉራጌም ፡ አገር ፡ እያነሰና ፡ እየተቀነሰ ፡ ሄደ ። ነገር ፡ ግን ፡ ጉራጌን ፡ ጋላ ፡ በዙሪያው ፡ ተሠርቶ ፡ ወደ ፡ ዜጋመልና ፡ ወዳንከበር ፡ ወደ ፡ ጐሠምና ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ወደ ፡ ሌላም ፡ ስፍራ ፡ ለትምርት ፡ እን ዳይሄድ ፡ ምንም ፡ ቢከለክለውና ፡ ቢያውከው ፡ እስካሰን ፡ እንጃበ ፡ ድረስ ፡ ስመ ፡ ክርስትናዉንና ፡ ሀብተ ፡ ወልድናዉን ፡ አላጠፋም ፡ ነበር ፤ ያላጠ ፋበትም ፡ ምክንያት ፡ ይኽ ነው ። ከቤተ ፡ ክህነት ፡ ወገን ፡ የሚወለደው ፡ በሰር ፡ ኹሉ ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በድንግልና ፡ እየኖረ ፡ ቄስ ፡ እከሌ ፡ ይባ ላል ፤ ከማይረባ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ይርቃል ፤ ሕፃናትን ፡ ያጠምቃል ። በዋሽ ፡ ውስጥ ፡ የተደበቀውንም ፡ ታቦት ፡ ያጥናል ፤ ይቀድሳል ፤ ያቈርባል ፤ ቀድ ሶም ፡ ስለ ፡ ቀርባን ፡ ክብር ፡ ታዝሎ ፡ ወይም ፡ በፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይገባል ፡ (ይመለሳል) ። ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ቅዳሜ ፡ ማታ ፡ ተሰብስ በው ፡ በቤተ ፡ ክሲያን ፡ ዐድረው ፡ እሑድ ፡ ቅዳሴ ፡ ውጪ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ይሄዳሉ ። መገበሪያ ፡ የሚኸነውንም ፡ ስንዴ ፡ የሚዘራውና ፡ የሚያርመው ፡ የሚያጭደውና ፡ የሚወቃው ፡ ባለሕግ ፡ ነው ፤ ከብትም ፡ እንዳይሸንበት ፡

በበትር ፥ ይወቃል ። ስላዚኽ ፥ በጉራጌ ፥ መሢዕት ፤ በሺዋ ፥ ሳታት ፤ በጐ ንደር ፥ ማሕሌት ፤ በጐጃም ፥ ጸሎት ፥ ይባላል ። ያም ፥ ቂስ ፥ መሞታው ፥ በደረሰ ፥ ጊዜ ፥ ርጥብ ፥ ስልጆ ፥ ይነፋና ፥ አስሮ ፥ ያኖራል ። እሱም ፥ ክሞ ተ ፥ በኺላ ፥ ሕዝቡ ፥ ተሰብስበው ፥ ወራሹን ፥ አቅርበው ፥ እግዜር ፥ የቂስ ፥ እከሌን ፥ ክህነት ፥ ያሳድርብኽ ፥ ይሉና ፥ ስልጆውን ፥ ፈተው ፥ ትንፋሹን ፥ በራሱ ፥ ላይ ፥ ያፈሱበታል ፤ እሱም ፥ ቂስ ፥ ይኾናል ። የማያስተምር ፥ ጳጳ ስ ፥ ካለበት ፥ ስፍራ ፥ ይልቅ ፥ የጉራጌ ፥ ቤተ ፥ ክህነት ፥ እጅግ ፥ የተቀደሰ ፥ ነው ። ቀድሞ ፥ ዘመንም ፥ በተጐለትና ፥ በወላዳ ፥ ቄላ ፥ ሚስቱ ፥ የሞተች በት ፥ ቂስ ፥ በሷ ፥ የሞተበትን ፥ የቂስ ፥ ሚስት ፥ አግብቶ ፥ እንደ ፥ ገና ፥ ሲ ቀድስ ፥ ይኖር ፥ ነበር ፥ ይባላል ። ይኽም ፥ የተደረገው ፥ በፍትሐ ፥ ነገሥት ፥ እንደ ፥ ተወሰነ ፥ ያ ፥ ቋንቋዉን ፥ የማያውቁትና ፥ ቋንቋቸውን ፥ የማያው ቅ ፥ የግብጥ ፥ ጳጳስ ፥ ተገዝቶ ፥ በማይመጣበት ፥ ጊዜ ፥ ነው ። ይኽንንም ፥ ጋብቻ ፥ የቆብ ፥ ተዝካር ፥ የለመዱ ፥ ሰዎች ፥ ይነቅፉት ፥ ይኾናል ። ትልቁ ፥ ቅዱስ ፥ አቡነ ፥ ተክለ ፥ ሃይማኖት ፥ በጉራጌ ፥ አገር ፥ እንዳስተማሩ ፥ ገድላ ቸው ፥ ይመሰክራልና ፤ ይኽች ፥ እውነተኛዋ ፥ የጉራጌ ፥ አምልክ ፥ የሳቸ ው ፥ ሳትኽን ፥ አትቀርም ። ዐሰን ፥ እንጃቦ ፥ ያላሰለማቸው ፥ አክሊልና ፥ ምሁር ፥ ናቸው ። ጉራጌ ፥ ሲተርት ፥ አይትማሰል ፥ አይትጋባ ፥ ይላል ።

ጳጳሱ ፥ የግብጥ ፥ ስለ ፥ ኾነ ፥ አገራችንን ፥ ቅኦጥር ፥ የሌለው ፥ ጕዳት ፥ አ ግኝቷታል ፤ ከጕዳቱም ፥ አንዱ ፥ ይኽ ፥ ነው ። በማሀል ፥ ሥላሴ ፥ ጊዜ ፥ ከወገዳ ፥ ፲፩ሰዎች ፥ ጐንደር ፥ ሂደው ፥ ቅስና ፥ ተቀብለው ፥ ሲመለሱ ፥ ሽ ፍቶች ፥ ፈንግለው ፥ ሸዉቸው ። ካ፲፩ቱም ፥ ፫ቱ ፥ ፬ጊዜ ፥ ተሸጠው ፥ በ፫ ኛው ፥ ያንከበር ፥ ነጋዴ ፥ ቢገዛቸው ፥ አምልጠው ፥ አገራቸው ፥ በገቡ ፥ ጊ ዜ ፥ ከ፫ቱ ፥ ፭ኛው ፥ የኔ ፥ ዘር ፥ ተምሮ ፥ ቂስ የኾነ ፥ ርጉም ፥ ይኹን ፥ ብለ ው ፥ ስለ ፥ ረገሙ ፥ ጐሸውሃ ፥ በሚባል ፥ አገር ፥ ል፮ጆቻቸው ፥ ፈደል ፥ ሳይ ቈጥሩ ፥ ይኖራሉ ። ርስታቸውንም ፥ ከሌላ ፥ መቅደስ ፥ መጥቶ ፥ ሲቆች ፥ ል ፮ጆቻቸውን ፥ ያገባ ፥ ዐማች ፥ ሲበላው ፥ ይኖራል ። (፲፬ኛ ፥ ሥዕል)

ማስረጃ ፥ ስሯጽ ፤ ግጥምና ፥ ታሪክ ፤ በግብጦች ፥ ፈንታ ፥ ሠለስቱ ፥ ምእትን ፥ ስለሚነቅፉና ፥ ስለሚያሙ ፥ ስለ ፥ ፍትሐ ፥ ነገሥት ፥ አንባቦችና ፥ ተርጓሞች ፥ ስለ ፥ ስሚዎችም ። (ከኪዳን ፥ ወል ድ ፥ ክፍል) ። ስምዐኒ ፥ አንባቢ ፥ ወእንግርከ ፤ ሰማዒኒ ፥ አሰምዕ ፥ ለከ ።

ደስታ ፥ ተክለ ፥ ወልድ ፥ በመራው ፥ ገበታ ፥
ያቀረብኹትን ፥ ቃል ፥ ባርኮላችኹ ፥ ጌታ ፤
ነገሩ ፥ ባቡን ፥ ወጥ ፥ እንዳበላላችኹ ፥
ኧንሆይ ፥ ይቁሙና ፥ ያሳልፉላችኹ ።
ከታሪኩ ፥ በፊት ፥ ግጥሙን ፥ ስትቀምሱ ፥
ወጡ ፥ ልንፍጪችኹ ፥ እንዳታንጥሱ ፤
በታሪኩም ፥ አለ ፥ ብዙ ፥ ሰናፍጭ ፥
ዐይን ፥ የሚያስለቅስ ፥ እንብ ፥ የሚያመነጭ ።
ስፈድና ፥ ወንፊት ፥ እያስ ፥ በሻችን ፥
ያልተንፋ ፥ ይቂት ፥ ምነው ፥ ማቡካታችን ፤
እስከ ፥ መቼ ፥ ድረስ ፥ እንጠጣለን ፥ ጕሽ ፥
እናጠራውሞይ ፥ በትርጓሜ ፥ ሻሽ ።
ኮሶው ፥ ንባብ ፥ ብቻ ፥ ስላላሻረኝ ፥
ቀጨሞ ፥ ጨምሬ ፥ ልደቅሰው ፥ ነኝ ።

እንደ ፣ አሮን ፣ ልጆች ፣ የኦሪትን ፣ ጣቃ ።
ለብሶ ፣ ተገናኘሮ ፣ የወንጌሎ ፣ አለቃ ፣
ፍትሐ ፣ ነገሥት ፣ አውጥው ፣ አባ ፣ ገብርኤል ፣
ግብጦችን ፣ ሲያንሣ ፣ እናንተን ፣ ሲዋል ፤
በስግኒያ ፣ ሺሕ ፣ ብር ፣ አራት ፣ ጳጳስ ፣
ገዝተው ፣ እንዳስመጡ ፣ ዐዬ ፣ ዮሐንስ ፤
ጳጳስና ፣ ክህነት ፣ በጠቢያው ፣ መንግሥት ፣
የንግድ ፣ ዕቃ ፣ ኹኖ ፣ እንዲሸጥለት ፤
ራሱን ፣ በሌዊ ፣ እኛን ፣ በይሁዳ ፣
መስሎ ፣ አነጻጽሮ ፣ ሱቁን ፣ ሲያስናዳ ፤
ባፀኛው ፣ አንቀጽ ፣ ቀለም ፣ ቀንዱን ፣ ተክሎ ፣
ኢይሠየሙ ፣ ሲል ፣ ኢያጸድስ ፣ ብሎ ፤
ፈራሽ ፣ ስው ፣ ሠራሽ ፣ ሕግ ፣ ስለ ፣ ጣፈባችኹ ፣
ሠለስቱ ፣ ምእትን ፣ ለምን ፣ ታማላችኹ ።
ካገር ፣ ልጆች ፣ በቀር ፣ ይኸንን ፣ ልቅና ፣
ባዕድ ፣ የውጪ ፣ አገር ፣ ሰው ፣ ይሾም ፣ መች ፣ አሉና ፤
ኢትዮጵያንስ ፣ ለይተው ፣ ከስልቅ ፣
መቼ ፣ ፈረዱና ፣ አሉታና ፣ ጽድቅ ፤
በስልቅ ፣ ፀይን ፣ ገመድ ፣ ቢስፈር ፣ ቢለካ ፣
ሦስት ፣ እጅ ፣ አይበልጥመይ ፣ የናንተ ፣ ስበካ ።
ግብጥ ፣ ያፈለቀውን ፣ አሉታ ፣ ጠበል ፣
ከሥሩ ፣ ከምንጩ ፣ ቅዱት ፣ በመንቀል ።
ያባ ፣ ገብርኤል ፣ ፍርድ ፣ ዕጥፍ ፣ ድርብ ፣ ግፍ ፣
ባጀ ፣ ዐንገት ፣ ላይ ፣ ዕንቅርት ፣ ከገቦሮ ፣ ደግፍ ፤
ወይም ፣ ትንባኾ ፣ ጠጭ ፣ ዛር ፣ ባለውኾሞ ፣
ኢያጸድስ ፣ የሚል ፣ መጠጣውን ፣ ሹሞ ፤
የዘርም ፣ ትርጓሜ ፣ በሌቦር ፣ ልሳን ፣
ፍስጥ ፣ ብዑድ ፣ ነኪር ፣ እምቤተ ፣ ክርስቲያን ።
የኒቅያን ፣ ግዝት ፣ እንዳባይ ፣ ጠጥቶ ፣
በጠቢያው ፣ ላይ ፣ ሲዋሽ ፣ አያፍርሞይ ፣ ከቶ ፤
ይሰበር ፣ ይሰበር ፣ ወዲያ ፣ ይሰበር ፣
ይኸ ፣ በጠቢያው ፣ ዐንገት ፣ የጣነው ፣ ቀንበር ።
የዘራውም ፣ ክርዳድ ፣ ገረማና ፣ ጌንጭ ፣
ከስንዴው ፣ መካከል ፣ ይታረም ፣ ይነጭ ።
ዐንገት ፣ መፈጠሩ ፣ ዙሮ ፣ ለማየት ፣
ራስንም ፣ ችሎ ፣ ጐገሥ ፣ ለመውጣት ፤
ራሱን ፣ የማይችል ፣ ዐንገት ፣ አያስው ፣
ምን ፣ ሰው ፣ ነው ፣ ምን ፣ ሰው ፣ ነው ፣ ረ ፣ ምን ፣ ሰው ፣ ነው
ራስ ፣ አለመቻል ፣ ባሕርያዊ ፣ ሕግ ፣
ለድዉይ ፣ ለሕፃን ፣ እስኪድን ፣ እስኪያደግ ።

ሠለስቱ ፣ ምእትስ ፣ በኒቅያ ፣ ሸንጎ ፣
የፈረዱልን ፣ ፍርድ ፣ ጤፍ ፣ እንጀራና ፣ ርጎ ፤
ዘወንጌላውያን ፣ ባራቱ ፣ እንሰሶች ፣
በኪሩቤል ፣ አምሳል ፣ በግዜር ፣ ፈረሶች ፤
ሊቃነ ፣ ጳጳሳት ፣ የወንጌል ፣ አፍላግ ፣
ካራት ፣ እንዳይወጡ ፣ ስላቆሙት ፣ ሕግ ፤
ምንም ፣ ለብጆችን ፣ እንዳንሾም ፣ በትረክ ፣
ኢይሚሙ ፣ ብለው ፣ ቢጥፉብን ፣ ልክ ፤
ለስልቅና ፣ ለኛ ፣ ለይተው ፣ በፍርድ ፣
አቁመውልናል ፣ ኹለት ፣ አዕማድ ፤
እንደ ፣ ያቁምና ፣ እንደ ፣ በለዝ ፣ ያሉ ፣
በወርድ ፣ በቁመት ፣ የተተካክሉ ።
ፍርዳቸውም ፣ ይኸ ፣ ነው ፣ ለግብጥ ፣ የሚገባ ፣
ሊቀ ፣ ጳጳስ ፣ መሾም ፣ ከኛው ፣ አንዱን ፣ አባ ፤
የአንጾኪያው ፣ ሊቅ ፣ ከስልቅ ፣ አንዱን ፣ ሰው ፣
ሊቀ ፣ ጳጳስ ፣ ብሎ ፣ እንደሚሾመው ።
ከኛም ፣ አንዱን ፣ መሾም ፣ ባጀኛው ፣ ሰላማ ፣
ዝምሮት ፣ ነበረ ፣ አትናቴዎስማ ፤
አላገኝም ፣ እንጂ ፣ መሳይ ፣ ተከታይ ፣
ዘመደቹ ፣ ታስረው ፣ በፍቅረ ፣ ንዋይ ።
እንዳትንፈራገጥ ፣ ላሚቱ ፣ አገራችን ፣
ወድሮ ፣ ያልባት ፣ ዘንድ ፣ በጐፍላ ፣ ስማችን ፣
ጳጳስ ፣ እስጥ ፣ ብሎ ፣ ግብጽ ፣ ካሎደረ ፣
ማነው ፣ እግር ፣ ተወርች ፣ ወንጌልን ፣ ያሰረ ።
ወንጌል ፣ ባገር ፣ ቋንቋ ፣ እንድትሰበክ ፣
አገርም ፣ ባገር ፣ ልጅ ፣ እንድትባረክ ፤
ከሺሚነት ፣ በቀር ፣ ተሹሞ ፣ መምጣት ፣
ለግብጽ ፣ አልተሰጠም ፣ ከሠለስቱ ፣ ምእት ።
የግብጽ ፣ ሰው ፣ ብቻ ፣ በዚያም ፣ በዚኽም ፣
በኹለት ፣ አህጉር ፣ አለቃ ፣ አይኾንም ፤
እንደ ፣ ስልቁ ፣ ጳጳስ ፣ ለኢትዮጲውም ፣
ሥልጣን ፣ አለውና ፣ ጳጳሳት ፣ ሊሾም ።
ጳጳሳት ፣ የማይሾም ፣ ለየወረዳው ፣
ሊቀ ፣ ጳጳስ ፣ ይባል ፣ አኅሉም ፣ አበው ።
ከስልቁ ፣ አሳንሰው ፣ የኢትዮጵያን ፣
ስም ፣ ብቻ ፣ አልሰጡትም ፣ እንበለ ፣ ሥልጣን ።
በስም ፣ ብቻ ፣ መክበር ፣ ሥራውን ፣ ሳይሠሩ ፣
የግብጦች ፣ ዱለት ፣ ነው ፣ መቼ ፣ የማኅበሩ ፤
በሀገራችንም ፣ ነብሪድና ፣ ዕጨጌ ፣
የጳጳሳት ፣ ስም ፣ ነው ፣ መቼ ፣ የባለጌ ፤
ከነጭ ፣ አባይ ፣ ወዲኽ ፣ ከማየ ፣ ግዮን ፣
ከበለው ፣ ከስናር ፣ እስከ ፣ ውጋጂን ፣
እስከ ፣ ወዲያ ፣ ማደም ፣ እስካረብ ፣ የመን ፣
እስከ ፣ ጀበል ፣ ሐበሽ ፣ እስከ ፣ ናግራን ፣
እንድትዘረጋ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣
ያስፈልጋልና ፣ መቶ ፣ ታምሳ ፣ አቡን ።

ንጻንት ፣ ከሌላት ፣ ክህነት ፣ በሀገሯ ፣
ፍጹም ፣ አይባልም ፣ የመንግሥት ፣ ክብሯ ፤
በባዕድ ፣ ጳጳስ ፣ እጅ ፣ ተቀብቶ ፣ መሾም ፣
ያሳዝናል ፣ እንጂ ፣ ደስ ፣ አያሰኝም ፤
ደስታም ፣ ቢኖረው ፣ ድርሻው ፣ ከ፱ ፣ አንድ ፤
ዘጠና ፣ ዘጠኙ ፣ ሂደ ፣ ወደ ፣ ባዕድ ።
ባዕድ ፣ ሐዋርያም ፣ ደስ ፣ ማሰኘቱ ፣
አስተምሮ ፣ እስኪሾም ፣ በጥንተ ፣ ስብከቱ ።
ለይቶ ፣ አለማወቅ ፣ ክብርና ፣ ጎላር ፣
ሲያስገዛን ፣ ይዋራል ፣ ጳጳስ ፣ እንደ ፣ ገብር ።
ኢታምልኩ ፣ ባዕደ ፣ የተባለው ፣ ቃል ፣
ስለ ፣ ጳጳሳትም ፣ ይተረጐማል ፤
ርሱ ፣ ባለቤቱ ፣ በዳዊት ፣ በገና ፣
አማልክት ፣ አንትሙ ፣ ብሏቸዋልና ።
ከእስራኤል ፣ በቀር ፣ አሕዛብ ፣ እንኳ ፣ እብዱ ፣
አያመልክም ፣ ነበር ፣ ያንዱን ፣ ጣዖት ፣ አንዱ ።
ንጉሥ ፣ ሳይኖራቸው ፣ ዖርያና ፣ አርመን ፣
መርጠው ፣ ይሾማሉ ፣ በትረክና ፣ አቡን ፤
ከወገኑ ፣ መርጠ ፣ ጳጳስ ፣ የማይሾም ፣
ከጠቢያችን ፣ በቀር ፣ ሌላ ፣ ሕዝብ ፣ የለም ።

ግብጽ ፣ እንደ ፣ እስራኤል ፣ ሳይከተለን ፣
የወሰድነውን ፣ ልብስ ፣ ከርሱ ፣ ተውሰን ፣
ለብስንማ ፣ ቢኾን ፣ ዐጥፈን ፣ ደርበን ፤
ስንኳን ፣ ካባይ ፣ ወዲኽ ፣ ግዛታችንን ፣
እንደ ፣ ስልቅ ፣ ሰዎች ፣ ጳጳስ ፣ እየሾምን ፣
እንሰብካት ፣ ነበረ ፣ ደቡብ ፣ አፍሪቃን ።
ያባቶቻችንን ፣ ፈረስና ፣ ጓዝ ፣
ባሕርም ፣ አሳገደው ፣ እንኳን ፣ ፈሳሽ ፣ ወንዝ ፤
ባለታሪኮችም ፣ ይመሰክራሉ ፣
ያማራ ፣ ቍራጮች ፣ ሞዛምቢክ ፣ እንዳሉ ።
በስሜን ፣ አፍሪቃም ፣ ያዬ ፣ ዳዊት ፣ ጫማ ፣
ሱዳንና ፣ ኖባን ፣ ሲረግጥ ፣ እንዳውድማ ፤
የግብጽን ፣ ጕረሮ ፣ አባይን ፣ መዝጋት ፣
በጣታቸው ፣ ነበር ፣ እንደ ፣ ቀለበት ።
ዛሬም ፣ እንደ ፣ ዳዊት ፣ በጥንቱ ፣ ስለባ ፣
ያፍሪቃን ፣ አህጉር ፣ ስናጥ ፣ ስናገባ ፣
አይበቃም ፣ ተብሎ ፣ አንድ ፣ ኾን ፣ ደረባ ፤
በንይለ ፣ ሥላሴ ፣ በቀዳማዊው ፣
ቀዳማዊ ፣ ኹኖ ፣ የተገፇመረው ፣
መፈጸሙ ፣ አይቀርም ፣ ኂላ ፣ በጊዜው ።
ዐምስቱን ፣ ጳጳሳት ፣ ሰዎች ፣ ኹሉ ፣ እንደኔ ፣
መስለዋቸዋል ፣ በዋዜማ ፣ ቅኔ ፤
ስሥነ ፣ በሳሉ ፣ ምንም ፣ ቢቸኩል ፣
ዋዜማ ፣ ሳይቆም ፣ አይከብርም ፣ በዓል ።
ነገር ፣ ሲበዛበት ፣ ልብ ፣ እንዳይዘነጋ ፣
አራተኛው ፣ እንቀጽ ፣ በዚኹ ፣ ይዘጋ ፤
አባ ፣ ገብርኤልም ፣ በያዘው ፣ ዐለንጋ ፣
መገረፉ ፣ አይቀርም ፣ ጨርሶ ፣ ሲነጋ ።
ባወጡት ፣ ዳኛና ፣ በያዙት ፣ በትር ፣
መረታት ፣ መመታት ፣ እንደኋት ፣ ያሳፍር ።
ያባቶቹ ፣ መዝገብ ፣ ቋንቋና ፣ ትምርት ፣
ዕልም ፣ ድርግም ፣ ብሎ ፣ እስኪጠፋበት ፤
ሺሕ ፣ ስባት ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ በንግድ ፣ ሲኖር ፣
ያተረፈው ፣ የለም ፣ ከማጉደል ፣ በቀር ።
በጠየቀው ፣ ጊዜ ፣ አቁሞ ፣ ከፊቱ ፣
ምን ፣ ይመልስ ፣ ይኾን ፣ ለባለመክሊቱ ።
ዮርያማ ፣ ባይኖር ፣ ጵጵስና ፣ ስጧ ፣
ጭራሽ ፣ ደርቆ ፣ ነበር ፣ የክህነቱ ፣ ምንጭ ፤
ከዚያው ፣ ከምንገዛው ፣ ካንዱ ፣ ጳጳስ ፣ ጐንጭ ፣
ዳግመኛ ፣ እየገዛን ፣ እንዳንጐነጭ ።
ዘሬም ፣ በየፈናው ፣ ተበታትኖ ፣ ሕዝቡ ፣
ፎጀ ፣ ሺሕ ፣ ነው ፣ ያለው ፣ በመዝገቡ ፤
ለፎጀው ፣ ሺሕ ፣ ባሥራ ፣ ስምንት ፣ ክፍል ፣
ዐሥራ ፣ ስምንት ፣ ጳጳስ ፣ ይሾምለታል ።
ቆቅ ፣ ማለዳ ፣ ጩኾ ፣ ወደ ፣ ርሱ ፣ አጠገብ ፣
ያሎለዳቸውን ፣ እንዲሰበስብ ፣
እኛንም ፣ ስብስቦ ፣ መዝሞን ፣ ቢኾን ፣
እናነግ ፣ ነበር ፣ ሠወስት ፣ መቶ ፣ አቡን ።

በግብጦች ፣ ሰንሰለት ፣ በወፍራም ፣ አሰታ ፣
የታሰረው ፣ ንባብ ፣ በጽድቅ ፣ እስኪፈታ ፤
ከናባ ፣ ገብርኤል ፣ እየተሻገተ ፣
በፍትሐ ፣ ነገሥት ፣ ውስጥ ፣ ዐይኑን ፣ ለክፈተ ፤
የግዝት ፣ ማየ ፣ አይጎ ፣ የርግማን ፣ በረደ ፣
እንሆ ፣ ይታያል ፣ በግብጽ ፣ ላይ ፣ ወርደ ።

ወፈታሒሰ ፣ ውእቱ ፣ ሊቀ ካህናት ፤ ወውእቱ ፣ ሊቀ ጳጳሳት ፤ አው ፣ ኤጲስቆጶስ ። ይኩን ፣ ድኵነ ፣ ምስማዕ ፣ ወንጻሬ ፣ ከመ ፣ ይፍልጥ ፣ ቃለ ፣ ጽድቅ ፣ ወቃለ ፣ ሐሰት ። ወይኩን ፣ ድኵነ ልሳን ፣ ወዘየአምር ፣ ነገረ ፣ ል ሳን ፣ እንተ ፣ ኢትትከሀል ፤ ልሳነ ፣ ሰብአ ፣ ሚመቱ ፣ በዘይትናገሩ ፣ በበይ

ናቲሆሙ ፡ (ፍ ፡ ነ ፵፫) ። ወለዚሁኒ ፡ ዘዐለወ ፡ ዘንተ ፡ ሕገ ፡ ሲናዖስ ፡ ያ ወግዘ ። አሌ ፡ ለቱ ፡ ለዘየዐሉ ፡ ዘንተ ፡ ሕገ ፤ ወሲናዖስ ፡ ያወግዘ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፬ ፡ ዘኊቅያ ፡ ፴፬ና ፡ ፫፯) ። ለዚኽ ፡ ቃል ፡ ማገገ ፡ (ገላ፭ ፡ ፮ ፡ ፱ ። ፭ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፮—፲፭ ። ሕዝ፳፱ ፡ ፯ ፡ ፮ ፡ ፲፭ ። ማቴ፮ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ። ፲፭ ፡ ፮ ፡ ፮ ፡ ፱ ፡ ፲፱ ። ነ፲ ፡ ፯) ።

(ታሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ስላለማወቅ)

በጐንደሮች ፡ መንግሥት ፡ ከላስታ ፡ ብዙ ፡ ዛቋኞች ፡ ጐንደር ፡ ወርደው ፡ በንባብ ፡ ከተፈ ተኑ ፡ በኂላ ፡ አምኝሩ ፡ ቅስና ፡ የሚሾሙትን ፡ ፪፪ብር ፡ ጉበ ፡ አምጡ ፡ ስላለ ፤ ኹሉ ፡ እንዳቅ ማቸው ፡ ሲሰጡ ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ድኽነቱ ፡ የለኝም ፡ ቢል ፡ ለይቶ ፡ አስቀረው ። ወንድሞ ቹ ፡ ቀሰው ፡ ሲወጡ ፡ በደጅ ፡ ቄይቶ ፡ ፪ጣቶቹ ን ፡ ባላ ፡ አስመስሎ ፡ ቀሰረና ፤ አባታችን ፡ እግ ዜር ፡ ያሳይዎ ፤ አምኝርዎ ፡ ለኔ ፡ ፪ብር ፡ ካልሰ ጠኽ ፡ አትቀስም ፡ ብሎ ፡ ከለከለኝ ፤ እንኳን ፡ ፪ብር ፡ ፭ብር ፡ የለኝም ፡ ፍጹም ፡ ድኻ ፡ ነኝ ፡ ሲል ፡ ሌባ ፡ ጣቱን ፡ ደግሞ ፡ ቀስሮ ፡ አሳየ ። አቡኑ ፡ ምን ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ አምኝሩን ፡ ቢጠ ይቅ ፤ ሚስቶቹ ፡ ፪ ፡ ናቸው ፤ ባንዲት ፡ ሴት ፡ መወሰን ፡ አልችልምና ፤ በኹለቱም ፡ ቅስና ፡ ይ ስጠኝ ፡ ይላል ፡ አለው ። ጳጳሱም ፡ ደንግጠ ፡ ፊቱን ፡ አማተበና ፡ የማሪያም ፡ ጠላት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ይኽን ፡ ያልመታ ፡ ብሎ ፡ ቁሞ ፡ አስ ደበደው ፤ ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ በዚኽ ፡ ከተማ ፡ ያደርኽ ፡ እንደ ፡ ኹን ፡ ወዮልኽ ፡ ተብሎ ፡ ከ ወንድሞቹ ፡ ተንጥሎ ፡ ደሙንና ፡ እንባዉን ፡ እያዘራ ፡ ወዳገሩ ፡ ተመልሶ ፡ ሄደ ፡ ይባላል ። ይኽም ፡ ታሪክ ፡ በውጪ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ተጥ ኽል ፤ ሌላም ፡ ይኽን ፡ የመሰለ ፡ ዐብሮት ፡ የተ ጣፈ ፡ ብዙ ፡ ያቡኖችና ፡ ያምኝሮች ፡ ግፍ ፡ አ ለ ። በመጨረሻውም ፡ ጸሓፊው ፡ የዚኽን ፡ ታ ሪክ ፡ ማስሮ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በውስጢ ፡ በጋጢ ፡ ከሚወለደው ፡ ፈረስ ፡ በቅሎ ፡ ያውም ፡ ከፎ ሌውና ፡ ከሠጋፋ ፡ ከድንጉላው ፡ ይልቅ ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ከብት ፡ ትወዳ ስች ፡ ብሎ ፡ በተረት ፡ መግላሊት ፡ ከድኖታል ።

ዛሬ ፡ ግን ፡ ባዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ቀርነት ፤ በወጣቶቿ ፡ ንብነት ፡ ባውራዋ ፡ በንይስ ፡ ሥላሴ ፡ መሪነት ፡ በግዙር ፡ አናቢነት ፡ ያገር ፡ ልጅ ፡ የ ማር ፡ እጅ ፡ መኽኑን ፡ ዐውቃ ፡ መላስና ፡ መ ቅመስ ፡ ገሥራሉች ። ከፋቅ ፡ ዘመድም ፡ ዐ ብሮ ፡ የሚሞት ፡ የቅርብ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ መብለጡ ንና ፡መሻሉን ፡ አለጥርጥር ፡ ዐውቃለች ።

ዓዲ ፡ ናቱሉ ፡ ወንዌስክ ፡ ጽሑፈ ፡ ካልእ ፡ ታሪክ ፡ ዘርቱዐ ፡ ይሰብክ ፤ በእንተ ፡ ብዝኀ ፡ ዕበያ ፡ ወፍድፋዴ ፡ ክብረ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እሞን ፡ ወእ ምሔውቶን ፡ ለአህጉረ ፡ ገነት ፡ አፍራቅያ ። ገነትሰ ፡ ምድረ ፡ ሠኸ ፡ አው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነቅዐ ፡ ማየ ፡ ላዮን ፡ ወኤፌሶን ፡ ዘይሰቅያ ፤ ትሰመይ ፡ ሰማየ ፡ እምትክት ፡ በልዕልናሃ ፡ እምአድባራት ፤ ወበአብጽሖተ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪሃ ፤ በከመ ፡ ጽሑፍ ። በፍልስጥዔም ፡ ያሉ ፡ የምሥራቆች ን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ርስት ፡ ከሚናገር ፡ ከሎንሶ ፡ ቢዮ ፡ ታሪክ ፡ በዐረብ ፡ ቋንቋ ፡ ጥርና ፡ አሳትሞ ፡ ከናረው ፡ ከኹለተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ወዳማርኛ ፡ የተቀዳ ፡ ፮ኛ ፡ ክፍል ። ከጥንት ፡ ዣሥሮ ፡ በቅድስት ፡ አገር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የነበረ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ርስትና ፡ ቦታ ፡ ይናገራል ፤ ሎንሶ ፡ ቢዮም ፡ ፮ቋንቋ ፡ የሚያውቅ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ባላባት ፡ ነው ። ተርጓሞቹም ፡ ኹለት ፡ ናቸው ፤ መጠሉን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ያመጣው ፡ ኪዳን ፡ ወልድና ፡ ዐረቢ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ በሐረ ር ፡ ከተማ ፡ ፲፱፻፲፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዘወትር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከሚኖሩ ፡ ክርስቲያ ኖች ፡ ጭ ምር ፡ ናቸው ፤ በኹለተኛው ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ተነገረ ።

ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ በቅድስት ፡ አገር ፡ ለሚኖሩ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡

ከሌሎች ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ነበራቸው ። ይኸውም ፡ ስለ፫ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ፩ኛ ፡ ቅድስቲቱ ፡ ቦታ ፡ በጃቸው ፡ ስለ ፡ ኾነች ። ፪ኛ ፡ በያመት ፡ ባሉ ፡ ፡ ከሌላው ፡ ሕዝብ ፡ እነሱ ፡ የሚቀድሙበ ትና ፡ የሚሠለጥኑበት ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ። ፫ኛ ፡ በዚኹ ፡ በሚመጣ ው ፡ ክፍል ፡ እንደሚታይ ፡ መጠን ፡ ንጉሣቸው ፡ ለፈረንሲስካን ፡ መነኰ ሳት ፡ የዋለውና ፡ ያደረገው ፡ ብዙ ፡ ርዳታ ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ ነው ። ከቀ ደሙ ፡ ትውልድ ፡ ቅድስቲቱን ፡ አገር ፡ ለመሳም ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ በጕዳናቸው ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መኖራቸው ን ፡ አብዝተው ፡ ይናገራሉ ። በ፲፫፻፬ ፡ ዓመት ፡ ፍልስጥኤምን ፡ ዙሮ ፡ ያየ ፡ አቡነ ፡ በሩካር ፡ ዶመኒካኒው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ጋ ራ ፡ አንድነት ፡ ያላቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ።

ዳግመኛም ፡ በ፲፬፻፴፪ ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የመጣ ፡ በሪትራ ንዱን ፡ ዱላብሩኪይር ፡ በነልጎታ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካሉት ፡ ክርስቲያኖ ች ፡ ጋራ ፡ ዘወትር ፡ የሚኖሩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ናቸው ፤ እለ ኹም ፡ ከ ዮሐንስ ፡ ቀሲስ ፡ አገር ፡ የመጡ ፡ ብሎ ፡ ይናገራል ። (ይኸውም ፡ ደብረ ፡ ሊባ ኖስ ፡ ይመስላል) ። ኸዋጃ ፡ (ሙሴ) ፡ ዱበሪፍም ፡ የፈረንሳዊ ፡ መልክተኛ ፡ በስጥንቡል ፡ ከተማ ፡ ነገር ፡ ጨራሽ ፡ የነበረው ፡ በሥራው ፡ መካከል ፡ ለ መፈረጅ ፡ ወደ ፡ ምሥሪቅ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ የአብርሃም ፡ መሠዊያና ፡ የ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ መሟሪት ፡ ማቅረቢያ ፡ የነበረውን ፡ ዛሬ ፡ በሮሞች ፡ (ግ ሪክኛ) ፡ እጅ ፡ ያለውን ፡ የኹለቱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በታ ፡ ሲተረጕ ም እንዲኽ ፡ ይላል ። ከዚያም ፡ ከወጣነ ፡ በኻላ ፡ ጨለማ ፡ ባለበት ፡ በብ ዙ ፡ ምድር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ ወልፈን ፡ በአብርሃም ፡ ስም ፡ ወደ ፡ ታወቀች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጣን ። ይችውም ፡ የተሠራችው ፡ አብርሃ ም ፡ ልጁን ፡ ሊሠዋ ፡ ባሰበበት ፡ በታ ፡ ላይ ፡ ነው ። መሬቱም ፡ ባማረ ፡ በ ተሸለመ ፡ በታናናሽ ፡ እብነ ፡ በረድ ፡ የተጸፈጸፈ ፡ ነው ፤ በዚያም ፡ ላይ ፡ የቱርክ ፡ ምንጣፍ ፡ ተነጥፎበታል ። መሬቱን ፡ የሚሳለም ፡ ሰው ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ምንጣፉን ፡ ያነሡለታል ። ከዚኽችም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስተኀ ላ ፡ ያለው ፡ ኢየሱስ ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ የተቀበለበት ፡ ደብረ ፡ ቀራንዮ ፡ ነ ው ፤ በመካከላቸው ፡ ከናስ ፡ ግንብ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለም ። ከዚያም ፡ የመ ልከ ፡ ጼዴቅ ፡ መሟሪት ፡ በታ ፡ ወደምትባል ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ ያገባል ፤ ያችም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እጅግ ፡ የተጌጠች ፡ ናት ፤ በር ሷም ፡ የሚያገለግሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ናቸው ። ከኹለቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ በንዲቱ ፡ ከነሱ ፡ ወገን ፡ የሚኸኑ ፡ ጥቂቀሮች ፡ መነኰሳይያት ፡ ነ በሩባት ፡ ይላል ። ዳግመኛም ፡ ይኸው ፡ ኸዋጃ ፡ ዱበሪፍ ፡ ኅልጎታን ፡ ስን

ሰለም ፣ የታነጠ ፣ የንጠት ፣ ደጃፍ ፣ ወዳላት ፣ ኢትዮጵያውያን ፣ ወደሚያ ገለግሏት ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ገባን ፤ የመንበሩ ፣ ዐምድ ፣ በቁርበት ፣ የተ ለበጠ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ እስከዚኽ ፣ ተናግሯል ። ፈረንሱአርኑድም ፣ የኽ ዋጃ ፣ ዱበሪፍ ፣ የመርከቡ ፣ አለቃ ፣ ባ፲፯፻፱ ፣ ዓመት ፣ ወደ ፣ ምሥራቅ ፣ የ ሄደበትን ፣ ታሪክ ፣ ሲጥፍ ፣ አብርሃም ፣ ልጁ ፣ ይስሐቅን ፣ ለመሠዋት ፣ በ ሰበበት ፣ በታ ፣ ላይ ፣ ያማረች ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ትገኛለች ፣ ይላል ።

እንደዚኽም ፣ ኹሉ ፣ ባ፲፯፻፳፱ ፣ ዓመት ፣ ወደየሩሳሌም ፣ የመጣ ው ፣ ከቡሽዊው ፣ አቡነ ፣ በሲፈክዱብሩፈንስ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ሰዎች ፣ በጎል ጎታ ፣ መኖራቸውን ፣ ይናገራል ። እነሱም ፣ በዚኹ ፣ ቦታ ፣ ላይ ፣ መስቀ ል ፣ በተተከለበት ፣ በቀራንዮ ፣ ቀስተ ፣ ደመና ፣ ሠርተዋል ። በቀስተ ፣ ደ መናውም ፣ ላይ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ አለች ፣ በኢትዮጵያ ፣ ጳጳስ ፣ እጅ ፣ ይ ላል ። «ሶርያ ፣ ከግብጥ ፣ ተጣልቶ ፣ ቶማስ ፣ የሚባል ፣ ኢትዮጵያዊ ፣ ለሐበሻ ፣ ገዳም ፣ ኤጲስ ቆጳስ ፣ ሹሞ ፣ ነበርና ፤ ጳጳስ ፣ ያለው ፣ ርሱ ፣ ይመስላል» ። ደግሞም ፣ ኸዋጃ ፣ ዱሪሻክ ፣ ባወጣው ፣ መጽሐፍ ፣ የሹማቸውን ፣ ታሪክ ፣ በተናገረበት ፣ በዛካሪስቲ ፣ ይ ታወቃል ። ያም ፣ የኢትዮጵያ ፣ መኰንን ፣ መካናት ፣ ቅዱሳትን ፣ ለመሳም ፣ ወደየሩሳሌም ፣ በመጣ ፣ ጊዜ ፣ ከኢትዮጵያ ፣ ገዳም ፣ ሰፈረ ። ዘወትር ፣ ከ ነሱ ፣ ብዙ ፣ ሕዝብ ፣ በዚኽ ፣ አገር ፣ ይገኙ ፣ ነበረና ፣ ይላል ። ኸዋጃ ፣ ዱቲፈኑም ባ፲፯፻፺፫ ፣ ዓመት ፣ ወደ ፣ ምሥራቅ ፣ በሄደበት ፣ መልእክቱ ፣ እ ንዲኹ ፣ ይላል ። ደግሞም ፣ ወደ ፣ ጎልጎታ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ግቢ ፣ መ ጣን ፤ ከቀራንዮ ፣ በስተቀኝ ፣ በትንሽ ፣ ደጃፍ ፣ ገብተን ፣ ፴፱ዕርከን ፣ ወ ጥተን ፣ ስንዘር ፣ በኢትዮጵያውያን ፣ እጅ ፣ ያሉ ፣ ፪ቤተ ፣ ክርስቲያኖች ፣ አ ገኘን ፣ ብሎ ፣ ይናገራል ። ይኸውም ፣ መጽሐፍ ፣ አውጪው ፣ እሱ ፣ ራሱ ፣ ይመሰክራል ። በኢዮሳፍጥ ፣ ወንዝ ፣ ካለች ፣ ከድንግል ፣ መቃብር ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ በስተግራ ፣ ወገን ፣ ያማረች ፣ የውሃ ፣ ጕድጓድ ፣ አለች ። በስ ተዠርባዋ ፣ ያለው የኢትዮጵያ ፣ መቅደስ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ይናገራል ። (ዛሬ ፣ ግን ፣ አርመንና ፣ ግብጥ ፣ ይዘውታል) ። የፈረንሲስካን ፣ መነኰሳት ፣ ወኪልም ፣ እ ስጥንቡል ፣ ከተማ ፣ ላለው ፣ ለፈረንሳዊ ፣ ሹም ፣ መካናት ፣ ቅዱሳትን ፣ ለማ ሳሰብ ፣ በጻፈው ፣ መልእክት ፣ እንዲኽ ፣ ይላል ። ለኢትዮጵያም ፣ ሰዎች ፣ በከተማው ፣ ገዳምና ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ አላቸው ። ከጎልጎታም ፣ ደጃፍ ፣ ከመውጫው ፣ ላይ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ነበራቸው ፣ እሷም ፣ ዛሬ ፣ በሮም ፣ እጅ ፣ ናት ፣ ብሎ ፣ ይናገራል ። «በዚኽ ፣ ታሪክ ፣ ውስጥ ፣ ሮም ፣ የሚለው ፣ ኹሉ ፣ ግ ሬክ ፣ ነው» ። ሮምና ፣ አርመን ፣ ግን ፣ በኢየሩሳሌም ፣ ያለ የሐበሾችን ፣ ይ ዘታ ፣ ለመቀማት ፣ ሲሻገቱ ፣ ነበሩና ፤ ርስታቸውን ፣ የተቀደሰና ፣ የሚሳም ፣ ቦታቸውን ፣ ኹሉ ፣ ከጃቸው ፣ ወሰዱባቸው ። ይኸውም ፣ የኢትዮጵያ ፣ ገ

ዳም ፡ ሙሐንድስ ፡ በስከዋል ፡ ሱራፌ ፡ ባሳየኝ ፡ ፈረማኖች ፡ ይታወቃል ። ከነዚኹም ፡ አንዲቱ ፡ በስላሞች ፡ ቊጥር ፡ ባ፲፪፻፷ ፡ ዓመት ፡ ዚልሕጃ ፡ በ ሚባል ፡ ባ፲፪፻ ፡ ወራቸው ፡ ባ፲፯ቀን ፡ የተጻፈች ፡ ናት ። ቃሏም ፡ ይኸ ፡ ነ ው ። በሲዩስ ፡ የሚባል ፡ የሮም ፡ በትረክ ፡ (ሊቀ ፡ ጳጳስ) ፡ ባ፲፻ ፡ ከ፷፬ ፡ ዓመት ፡ ዚልቂዕዳ ፡ በሚባል ፡ ባ፲፻ ፡ ወራቸው ፡ ባ፲ቀን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝቦች ፡ ከዳኝነቱ ፡ በታች ፡ ይደሩ ፡ የሚል ፡ ትእዛ ዝ ፡ ከሥልጣን ፡ ተቀበለ ፡ ትላለች ። እሱም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከቃዲው ፡ የአ ርመንን ፡ ሕዝቦች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉትን ፡ ሊያቀርብለት ፡ ፈለገ ። የሐ በሾችን ፡ ወቅፍና ፡ የሚሰም ፡ ቦታቸውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸውን ፡ በጎ ልጎታ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ከውጪም ፡ ያለውን ፡ በጃቸው ፡ የያዙትን ፡ ኹ ሉ ፡ በሥልጣን ፡ ትእዛዝ ፡ ለቀው ፡ ለርሱ ፡ ያስረክቡ ፡ ዘንድ ። አገረ ፡ ገ ዥውም ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ኹላቸውን ፡ የአርመኖችን ጳጳስ ፡ ወኪል ፡ ት ርጁማናቸው ፡ የሚኸን ፡ የኸዘርን ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብን ፡ አቀረበለት ። ትእዛ ዙን ፡ ካነበበላቸው ፡ በኋላ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የነበረውን ፡ ኹሉ ፡ በ ጃችኹ ፡ ያለውን ፡ ለሮም ፡ አስረክቡ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ወዲያው ፡ የመ ንግሥት ፡ ሹማምቶች ፡ ወደ ፡ ጎልጎታ ፡ ሄዱ ፤ የሮሞች ፡ ትርጁማን ፡ አብ ራሂም ፡ በጎልጎታ ፡ ከሚኖረው ፡ ከሰርኪስ ፡ ከአርመኑና ፡ ከወገኖቹ ፡ በሹ ማምቱ ፡ ፊት ፡ ተረከበ ። ከግንዘቱ ፡ ላይ ፡ ቀንዲል የሚሰቀልበትን ፡ ቦታ ፡ ከመቃብሩ ፡ ውስጥ ፡ ፯ቀንዲል ፡ የሚሰቀልበትን ፡ ቦታ ፤ ከመቃብሩም ፡ ው ጪ ፡ ፪ቀንዲል ፡ የሚሰቀልበትን ፡ ቦታ ፤ አንዱ ፡ በሰሜን ፡ አንዱ ፡ በ ደቡብ ፤ ፫ቱንም ፡ ጓዳዎች ፡ ለሐበሾች ፡ ብቻ ፡ የነበሩትን ፤ በቤተ ክርስ ቲያኑ ፡ ደቡብ ፡ ያሉትን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንነት ፡ የታወቁት ን ፡ በውስጣቸውም ፡ ያሉትን ፡ የብርጭቆ ፡ ቀንዲሎች ፤ በሰሜንም ፡ ያሉ ትን ፡ ፪ጓዳዎች ፡ እነሱን ፡ ተጠግቶ ፡ የታነጠውንና ፡ የተጌጠውን ፡ ዕንጨ ት ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ያለውን ፤ በምሥራቅም ፡ ያለውን ፡ መቅደስ ፡ የሐ በሾች ፡ መኸኑ ፡ የታወቀውን ፡ የታነጠ ፡ ዕንጨት ፡ በስተደቡብ ፡ በአንጻ ሩ ፡ ያለውን ፤ በምሥራቅና ፡ በደቡብ ፡ መካከል ፡ ያለውንም ፡ መቅደስ ፡ መንበሩ ፡ በሚሰለሙት ፡ ወምድ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፤ በውስጡም ፡ ያሉትን ፡ የብርጭቆ ፡ ቀንዲሎች ። ደጃፉ ፡ የታነጠ ፡ የተበሳሳ ፡ ዕንጨት ፡ የኸነውን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለውን ፤ ይኸ ፡ ኹሉ ፡ ከጎልጎታ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ው ስጥ ፡ ነው ። ኹሉንም ፡ ጨርሰው ፡ ወሰዱ ። በጎልጎታ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ለነበሩ ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ሰዎች ፡ ከብር ፡ ቀንዲልና ፡ ከብር ፡ መስቀላቸው ፡ ከንዋየ ፡ ቅድሳታቸው ፡ ኹሉ ፡ ምንም ፡ አልቀረላቸው ። ሐ በሾች ፡ ፯ቀንዲል ፡ ይሰቅሉበት ፡ በነበረው ፡ ቦታ ፡ ሮሞች ፡ ከራሳቸው ፡ ፰ ፡

የተበሳሳ ፥ የብር ፥ ቀንዲል ፥ ሰቀሉ ። ፯ቱን ፥ ከመቃብሩ ፥ ውስጥ ፥ አንዱ ን ፥ ከግንዘቱ ፥ ላይ ። በጎልጎታ ፥ የሚኖሩ ፥ ኢትዮጵያዊው ፥ መኹና ፥ ሶር ያዊው ፥ ዮሴፍ ፥ እንዲኽ ፥ ብለው ፥ ጽፈዋል ፥ ይባላል ። ከግንዘቱ ፥ ላይ ፥ ለሐበሾች ፥ የብር ፥ ቀንዲል ፥ ነበራቸው ፤ አርመኖች ፥ ወሰዱት ፤ የኢት ዮጵያ ፥ ቦታ ፥ በጃቸው ፥ ነበረና ። ሮሞች ፥ ደግሞ ፥ ካርመኖች ፥ የኢትዮጵ ያን ፥ ቤተ ፥ ክርስቲያን ፥ የታችኛይቱን ፥ በደቡብ ፥ በኩል ፥ ያለችውን ፥ ለ ጎልጎታ ፥ የምትጎራበተውን ፥ ወሰዱ ። በጎልጎታ ፥ ቤተ ፥ ክርስቲያን ፥ ውስ ጥ ፥ ወደ ፥ ርሷ ፥ የሚገቡባትንም ፥ የኢትዮጵያን ፥ ገዳም ፥ ከርሷም ፥ ጋራ ፥ ያለውን ፥ ቦታቸውንና ፥ ቤቶቻቸውን ፤ ከገዳሙም ፥ አጠገብ ፥ ከላይኛው ፥ ቤተ ፥ ክርስቲያን ፥ ውስጥ ፥ ያለውን ፥ ኹሉ ፥ ጠርሰው ፥ ወሰዱ ። ለኢ ትዮጵያ ፥ ሰዎች ፥ በጎልጎታ ፥ እንዲኽ ፥ የተደላደለ ፥ ቦታና ፥ መዓርግ ፥ ነበ ራቸው ። ብርሃን ፥ በሚወጣበት ፥ ቅዳሜ ፥ ከሚሰበሰቡት ፥ ኹሉ ፥ አስቀድ ሞ ፥ ወደ ፥ መቃብር ፥ የሚገባው ፥ የኢትዮጵያ ፥ ራኢስ ነው ፤ ለዚኹም ፥ እንሆ ፥ ፈረመናቸው ። ዚልህጃ ፥ ፲፱ቀን ፥ ፱፱፻፱፱ ፥ ዓመት ፥ ብርሃን ፥ ወደ ሚወጣበት ፥ ቦታ ፥ መዣመሪያ ፥ የሚገባ ፥ የኢትዮጵያ ፥ ራኢስ ፥ ነው ። ፪ ኛው ፥ የሮም ፥ በትረክ ። ፫ኛው ፥ የአርመን ፥ ራኢስ ። ፬ኛው ፥ የኵርጅ ፥ ራኢስ ። ፭ኛው ፥ የሶርያ ፥ ራኢስ ። ፮ኛው ፥ የግብጥ ፥ ራኢስ ፥ ነው ፥ ይላ ል ። በሌላውም ፥ ሕጂ ፥ እንደዚኹ ፥ ይላል ። ጀማደ ፥ እልአወል ፥ ፬ቀን ፥ ፱፱፷፫ ፥ ዓመት ፥ የኢትዮጵያ ፥ ክርስቲያኖች ፥ ራኢስ ፥ የተክለ ፥ ሃይማኖ ት ፥ ልጅ ፥ ዐብድ ፥ እልመሲሕና ፥ የሮሞች ፥ በትረክ ፥ ጀርማኖስ ፤ የአርመ ኖች ፥ ራኢስ ፥ የአብርሃም ፥ ልጅ ፥ እንድርያስ ፤ የኵርጅ ፥ ራኢስ ፥ የዳዊት ፥ ልጅ ፥ ዩአቄም ፤ የሶርያ ፥ ራኢስ ፥ የሐዲድ ፥ ልጅ ፥ ኤበይድ ፤ የግብጦች ፥ ራኢስ ፥ የዮሐንስ ፥ ልጅ ፥ ሚካኤል ፥ በቅድስት ፥ አገር ፥ በኢየሩሳሌም ፥ የ ሚኖሩ ፥ ተብሎ ፥ አስቀድሞ ፥ እንደ ፥ ተነገረ ፥ እነዚኽ ፥ ኹሉ ፥ ከዛሬ ፥ ቀ ን ፥ ዠምረው ፥ ወደ ፥ ፊት ፥ እንደ ፥ ጥንት ፥ እንዳለፈው ፥ ዘመን ፥ አገር ፥ ሳ ይከፈት ፥ እንደ ፥ ነበረው ፥ ሥርዐታቸው ፥ ሊሠሩ ፥ ተሰማሙ ። ከዚያም ፥ በኂላ ፥ በያመት ፥ ባላቸው ፥ ቀን ፥ ብርሃን ፥ በሚወጣበት ፥ ጊዜ ፥ በጎልጎ ታ ፥ መቅደስ ፥ ውስጥ ፥ አንድነት ፥ ይሰበሰባሉ ። ብርሃን ፥ ከሚወጣበት ፥ ቦታ ፥ መዣመሪያ ፥ የሚገባው ፥ የኢትዮጵያ ፥ ራኢስ ፥ (መምህር) ፥ ነው ፤ ከርሱም ፥ በኂላ ፥ የሮም ፥ በትረክ ፥ ነው ፤ ፫ኛው ፥ የአርመን ፥ ራኢስ ፤ ፬ ኛው ፥ የኵርጅ ፥ ራኢስ ፤ ፭ኛው ፥ የሶርያ ፥ ራኢስ ፤ ፮ኛው ፥ የግብጥ ፥ ራ ኢስ ፥ ነው ። ይኽም ፥ የጥንት ፥ ሥርዐታቸው ፥ ነው ። እነሱም ፥ እኹን ፥ ከ ተናገርነው ፥ ቦታ ፥ አንድነት ፥ ጧፍ ፥ አቃጥለው ፥ ከዚያ ፥ ይወጣሉ ። ደ ግሞም ፥ ብርሃን ፥ በሚወጣበት ፥ ቅዳሜ ፥ ከሚሰበሰቡት ፥ ዋነኛው ፥ የኢ

ትዮጵያ ፡ ቄስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይገለጣል ። ኡጂን ፡ ሩጂ ፡ በሚባል ፡ በፔኛ ው ፡ መጽሐፍ ፡ የምናነበው ፡ እንሆ ፡ ይኸ ፡ ነው ። በትረኩና ፡ ጳጳሳቱ ፡ ቀ ቀሳውስቱና ፡ መነኰሳቱ ፡ አንድነት ፡ ተሰብስበው ፡ ልብሰ ፡ በዓላቸውን ፡ ይለብሳሉ ፤ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ መቃብሩ ፡ ሲሄዱ ፡ አንድ ፡ ቄስ ፡ በፊት ፡ በፊታቸው ፡ ይሄዳል ። እሱም ፡ ለዚኹ ፡ ላመት ፡ ባል ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ከኢ ትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ከዮሐንስ ፡ ቀሲስ ፡ የሚላክ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ነው ። ይኸም ፡ የተናገርነው ፡ ቄስ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ይለብስና ፡ ዘይት ፡ የ መላበት ፡ ያልተቃጠለ ፡ ፈትል ፡ ያለበት ፡ የብርጭቆ ፡ ቀንዲል ፡ በኺ ፡ ይ ዞ ፡ ወደ ፡ መቃብሩ ፡ ሲደርስ ፡ እስላሞች ፡ ይከፍቱለትና ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ፤ ገብቶም ፡ ደጃፉን ፡ ይዘጋል ። የሮም ፡ በትረክና ፡ የቀሩት ፡ ቀሳ ውስት ፡ ግን ፡ ከሕዝባቸው ፡ ጋራ ፡ በየጃቸው ፡ ጧፍ ፡ ይዘው ፡ ከውጪ ፡ ቁመው ፡ ይጠበቁታል ። ይኸውም ፡ ቄስ ፡ ብርሃን ፡ ከወጣለት ፡ በኋላ ፡ የ መቃብሩን ፡ ደጃፍ ፡ ይመታዋል ፤ የሚጠብቁት ፡ ሰዎች ፡ ለመሰለም ፡ ይ ገቡ ፡ ዘንድ ። የሮም ፡ በትረክና ፡ የቀሩት ፡ ሙጥራኖች ፡ በየጃቸው ፡ የያ ዙትን ፡ ጧፍ ፡ ከዚያ ፡ ቀንዲል ፡ አቃጥለው ፡ ወዲያው ፡ ፈጥነው ፡ ከመቃ ብሩ ፡ ይወጣሉ ። የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ብርሃን ፡ እያወጡ ፡ ርስታቸው ን ፡ በጃቸው ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ እስካ፲፯፻፩ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ነበሩ ። በ ትሪሙኒዩሲራፊኩ ፡ የሚባል ፡ ባለታሪክ ፡ እንዲኽ ፡ ይላል ፤ የምስር ፡ መ ንግሥት ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ ያባይን ፡ ዳር ፡ ድንበር ፡ የሚገዙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ውሃውን ፡ መመለስ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ማፍሰስ ፡ ከዚኽ ፡ የተነሣ ፡ ግብጥን ፡ እንድትራብና ፡ እንድትጠማ ፡ ማድረግ ፡ የሚቻላቸው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከምስር ፡ ንጉሥ ፡ የሚገባቸውን ፡ ዅሉ ፡ አገኙ ። ቅድስት ፡ በ ዓላቸውን ፡ እንደ ፡ ወትሮ ፡ ያከብሩ ፡ ዝመር ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ዘ መን ፡ ሠልጥነውባት ፡ ኖሩ ። ሌላውን ፡ መቀማት ፡ የማይችሉ ፡ ሮሞች ፡ ግን ፡ ሐበሾችን ፡ ጠላት ፡ አደረጓቸው ። ይኾን ፡ ተልእኳቸውን ፡ ቀምተ ው ፡ ለራሳቸው ፡ ሊያደርጉ ፡ ስለ ፡ ፈለጉ ፡ ታላቅ ፡ ሙግት ፡ አነሡባቸው ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ እስኪያከስሯቸው ፡ ድረስ ። በመጨረሻውም ፡ ዛሬ ፡ ዕርቅ ፡ አድርገው ፡ የሮም ፡ በትረክና ፡ ያርመን ፡ ጳጳስ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ቄስ ፡ ካንዱ ፡ ወይም ፡ ከኾላቱ ፡ ጋራ ፡ ኾነው ፡ በዓላቸውን ፡ ያከብራሉ ። ሮምና ፡ አ ርመን ፡ ከሐበሻ ፡ ጋራ ፡ ከመቃብሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ እንደ ፡ ጥንት ፡ ሥርዐታቸው ፡ ደጃፉን ፡ ዘግተው ፡ ብርሃን ፡ ያወጣሉ ። ሐበሾች ፡ ከ ሮምና ፡ ከርመን ፡ ጋራ ፡ ኾነው ፡ ከመቃብሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ብርሃ ን ፡ ማውጣታቸው ፡ የቀረበትን ፡ ጊዜ ፡ ለይቼ ፡ አላወቅኹትም ። (ስጽጽ) ባ፲ ፮፻፲፰ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በታችና ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ፱ኛው ፡ ሰክል ፡ ሲጨረስ ፡ በዚያ ፡ ግድም ፤ የቅዳሜ ፡ ዅር ፡ ለት ፡ ሮምና ፡ አርመን ፡ ብርሃን ፡ ስለ ፡ ማውጣት ፡ በቅድምና ፡ ነገር ፡ ተጣልተ